2) የፍጥረትን ታሪክ ማወቅ ሰውን ወደ ደኅንነት ለመምራት በቂ ይመስልሃል? ግለጽ።

ሠ. 1) በዘፍ. 1 ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋና ትምህርቶች ምንድናቸው?

2) ይህ ክፍል ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ስላለው ግንኙነት ምን ያስተምራል?

3) ይህስ በዛሬው ሕይወታችን ውስጥ የሚታየው እንዴት ነው?

ረ. 1) በሰው ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር አምሳል ምንድነው?

2) ይህ በሕይወታችን ውስጥ የሚታየው እንዴት ነው?

3) እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን በፈጠራቸው ጊዜ ከነበረው አምሳል፥ የአሁኑ የሰው ሁኔታ የሚለየው እንዴት ነው?

4) በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙትን የአጉል ጥላቻ አመለካከቶች ምሳሌዎች ዘርዝር።

5) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙትን የአድልዎ ምሳሌዎች ዘርዝር።

6) በውስጥዋና በኢትዮጵያ የሚገኘውን አድልዎ ለማስወገድ ቤተ ክርስቲያንህ ምን እያደረገች ነው?

ሰ. እግዚአብሔርን ስለ ፍጥረቱ የምታመልክበት የተወሰነ ጊዜ መድብ።

5. ጸሎት።

ትምህርት ሦስት

ዘፍ. 2፡4-4፡26

የመጀመሪያ ቀን፡- ዘፍ. 2፡4-25

ባለፈው ሳምንት ዘፍ. 1-2፡3 አጥንተናል። እነዚህ ጥቅሶች እግዚአብሔር ዓለምን እንደፈጠረ የተሰጠውን ጠቅለል ያለ ትምህርት ያቀርባሉ። ዛሬ በዓለም ውስጥ የሚታየውን ነገር ሁሉ እግዚአብሔር እንዴት በ6 ቀናት ውስት እንደ ፈጠረ ያስተምራሉ።

1ኛ ጥያቄ፡- ሀ) እግዚአብሔር በእያንዳንዱ ቀን የፈጠራቸውን ነገሮች ዘርዝር። ለ) እግዚአብሔር በሰባተኛው ቀን ምን አደረገ?

የዘፍጥረት ም.1 አብይ ዓላማ የፈጣሪ አምላክን ታላቅነት ማሳየት ነበር። እርሱ፥ በኃያል ቃሉ፥ ዛሬ የሚታየውን ነገር ሁሉ ፈጥሯል። ጸሐፊው ለእስራኤላውያን ሁለት አበይት ትምህርቶችን እንዴት ለማስተማር እንደ ሞከረም ተመልክተናል። በመጀመሪያ፥ ጸሐፊው እግዚአብሔር በነገሮች ሁሉ ላይ እንዴት ገዥ እንደሆነ ለማሳየት ሞክሯል። በፍጥረትም ሆነ በሰው ልጅ ሁሉ ላይ እግዚአብሔር ገዥ ነው። ገዥነቱም ከፈጣሪነቱ የተነሣ ነው። ፍጥረቱ እንደ መሆናችን፥ እግዚአብሔር በሕይወታችን ውስጥ በሚፈጸሙ ነገሮችም ላይ ገዥ ነው።

2ኛ ጥያቄ፡- ዛሬ እግዚአብሔር ገዥነቱን በሕይወታችን ውስጥ የሚገልጸው እንዴት ነው?

ሁለተኛ፥ ጸሐፊው ለእስራኤላውያን እግዚአብሔር ብቻ አምላክ እንደሆነ ለማስተማር ፈልጎ ነበር። ከዋክብትም ይሁኑ፥ ወይም ዛፎች፥ ወይም እንስሳት፥ የአሕዛብ አማልክት በሙሉ የሐሰት አማልክት ናቸው። ሁላቸውም የተፈጠሩ ነገሮች እንጂ አምላክ አይደሉም። ሁሉንም ነገር የፈጠረውና የእስራኤላውያን አምላክ የሆነው አንድ ጌታ እግዚአብሔር ብቻ አለ። ይህም ለእስራኤልውያን ይረዱት ዘንድ በጣም የሚያስቸግራቸው ትምህርት ነበር። በብሉይ ኪዳን ታሪካቸው ሁሉ በፈጣሪ ፈንታ ፍጥረትን ሲያመልኩ እናገኛቸዋለን። የውሸት አማልክትን አምልከዋል። ለምሳሌ በሲና ተራራ የወርቅ ጥጃ ምስል ሠርተው ማምለክ ጀምረዋል። በባቢሎናውያን እስከተማረኩበት ጊዜ ድረስ እስራኤላውያን ሐሰተኛ አማልክትን ማምለክ እንደሌለባቸው አልተማሩም ነበር።

3ኛ ጥያቄ፡- ዛሬም ለሰዎች እውነተኛውን አምላክ ማምለክ እጅግ የሚከብዳቸው ለምንድነው?

ዘፍ. 2፡4-25 በፍጥረት ላይ ሌላ አመለካከት አለው። ይኸውም በፍጥረት ጠቅላላ ታሪክ ላይ ከማተኮር ይልቅ፥ በሰው ፍጥረት ላይ

ያተኩራል። ስለ አዳምና ሔዋን አፈጣጠር፥ ስለ መጀመሪያ ቤታቸው ስለ ዔደን ገነት የበለጠ ይገልጻል።

4ኛ ጥያቄ፡- ዘፍ. 2፡4-25 አንብብ። ሀ) ሰው ከመፈጠሩ በፊት የነበረችው ምድር የተገለጸችው እንዴት ነው?

ለ) የሰውን አፈጣጠር በተመለከተ፥ በዘፍጥረት 1 ሳይጠቀስ በዘፍጥረት 2 ውስጥ የምናገኘው ተጨማሪ መረጃ ምንድነው?

ሐ) የዔደን ታላቅነት የተገለጸው እንዴት ነው?

መ) በአትክልቱ ውስጥ የነበሩ ሁለት የተለዩ ዛፎች ምንና ምን ነበሩ?

ሠ) የሁለቱ ዛፎች መኖር ዓላማ ምንድን ይመስልሃል?

ረ) አንድኛዋን ዛፍ በተመለከተ እግዚአብሔር የሰጠው ትዕዛዝ ምን ነበር?

ሰ) በዔደን የአዳም ኃላፊነቶች ምን ምን ነበሩ?

ሸ) እግዚአብሔር አይቶ ‹መልካም አይደለም› ያለው ምን ነበር?

ቀ) መልካም ያልነበረውን ነገር መልካም ለማድረግ፥ እግዚአብሔር ምን አደረገ?

በ) ከዘፍ. 2፡18-25 ጋብቻን በተመለከተ የመመሪያዎችን ዝርዝር አዘጋጅ።

ጸሐፊው በዘፍጥረት 2 ውስጥ በአእምሮአችን ለመሳል የሚፈልገው ምስል እግዚአብሔር እንዴት ሰውን በቂ ውኃ፥ ምግብ፥ ውበት፥ ወዘተ. በነበረበት ፍጹም የተለየ ሥፍራ እንዳስቀመጠው ነው። ሰው አፍቃሪ ፈጣሪውን የማይታዘዝበት ምንም ምክንያት አልነበረውም። ሰው ግን እግዚአብሔርን ሳይታዘዝ ቀረ። ጸሐፊው ይህ ያስከተላቸውን ታላላቅ መዘዞች ያሳይል (ምዕራፍ 3)።

1) እግዚአብሔር ሰውን ከመፍጠሩ አስቀድሞ የነበረችው ዓለም (2፡4-6)።

ጸሐፊው ስለ ሰው መፈጠር የሚናገረውን ዘገባ የሰው ልጅ ከመፈጠሩ አስቀድሞ ይጀምራል። እንደውም እግዚአብሔር ዕፅዋትን ሳይፈጥር በፊት ወደ ነበረው ወደ ሦስተኛው የፍጥረት ቀን ይመለሳል። ዕፅዋቱ ውኃ የሚያገኙት ከወንዞች፥ ከምንጮችና ከጤዛ ነበር። በኖኅ ዘመን እስከተገለጸው የጥፋት ውኃ ድረስ ስለ ዝናብ የተጻፈ ነገር የለም።

ይህ የጥንቱ ዓለም የተጀመረው ለሰው ልጅ መኖሪያነት የማይመች ሆኖ ነው። ዝናብ ስላለነበር፥ አትክልት አልነበረምና ለሰውም የሚበላው ምግብ አልነበረውም። ዳሩ ግን እግዚአብሔር ምድርን ለሰው ልጅ የማዘጋጀቱን ሂደት ጀምሯል። ምድርን በማዘጋጀት ሂደት ውስጥ የመጀመሪያው ደረጃ ለተክሎችና ለሰዎች ትክክለኛ የውኃ አገልግሎት ማዘጋጀት ነበር። ስለዚህ እግዚአብሔር ምድርን ለማጠጣት ከመሬት ውስጥ ምንጮችን አፈለቀ። ይህም ዕፅዋትን ለማብቀል ይችል ነበር።

2. የመጀመሪያው ሰው፥ የአዳም መፈጠር (2፡7)

በዘፍጥረት 1 እግዚአብሔር ወንድና ሴትን በአራሱ አምሳል እንደ ፈጠረ ብናነብም፥ እግዚአብሔር ሰውን እንዴት እንደፈጠረ በግልጽ አልተጠቀሰም። በዘፍጥረት 2 ውስጥ ግን ስለ ሁለቱም ወንድ (2፡7) እና ሴት (2፡21-23) አፈጣጠር የተሰጠ ዝርዝር ገለጻ እናነኛለን።

እግዚአብሔር ሰውን ለመፍጠር ያደረጋቸው ሁለት አበይት ነገሮች አሉ፡- በመጀመሪያ፥ እግዚአብሔር የምድርን አፈር በመውሰድ የሰውን ሥጋዊ ሰውነት አበጀው። ‹አበጀው› የሚለው ቃል ሸክላ ወስዶ ማድጋ ለሚያበጅ የሸክላ-ሠሪ የሚያገለግል መሆኑን መረዳቱ በጣም አስደናቂ ነው። እግዚአብሔር እንደ ሸክላ-ሠሪ ሆኖ ተገልጾአል። በዚህ ገለጻ አማካይነት ጸሐፊው ለማሳየት የሚሞክራቸው ሁለት አበይት ነገሮች አሉ።

1. ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ቢፈጠርም እንኳ፥ ከእግዚአብሔር በብዙ ርቀት የተለየ ነው። እንስሳትም ከአፈር የተፈጠሩ በመሆናቸው ሰው እንደ እንስሳት ዓይነት ነው (2፡19)። የሰው አካል አፈጣጠር ከእንስሳት ጋር ይመሳሰላል፤ ለዚህም ነው ሳይንቲስቶች ሰውን ከእንስሳት ክፍል፥ በተለይም ከአጥቢዎች ወገን የሚመድቡት። በሙሴ ዘመን፥ መሪዎች እራሳቸውን እንደ

አማልክት ለመቁጠር ሞክረው ነበር። ይህ ግን ማንነታቸውን በእርግጥ የሚያስታውሳቸው ነበር። እንደሌሎች ሰዎች ሁሉ እነሱም ከምድር አፈር የተበጁ ነበሩና። በዛሬው ዓለም ውስጥ፥ ሰውን እንደ ትልቅ ነገር ለማጋነን የሚፈልጉ በርካታ ሰዎች አሉ። እነዳንዶች እንዲያውም ሰው ‹አምላክ› ነው እያሉ ናቸው። ዳሩ ግን ይህ የጸሐፊው ገለጻ የማንነታችን አስታዋሽ በመሆኑ ራሳችንን ዝቅ አድርጎ ወደማሳየት ሊመራን ይገባል። ልክ እንደሸክላ ሁሉ፥ ጥንቃቄ የሚያሻን፥ ተሰባሪዎችና ደካሞች ነን።

5ኛ ጥያቄ፡- ይህ በሕይወትህ እንዴት ይታያል?

እንደሥጋዊ ሰው፥ ሰው ከምድር አፈር ተፈጥሯል። በኋላ አዳምና ሔዋን በኃጢአት ውስጥ በመውደቃቸው፥ የሰው ሥጋዊ ሰውነት በሞት ወደመጣበት አፈር ሲመለስ እንመለከታለን።

2. ሰውን በማበጀቱ ሂደት ውስጥ እግዚአብሔር የተለየ ጥንቃቄ አድርጓል። ልክ ሸክላ-ሠሪው ቆንጆ ሸክላ ለመሥራት ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት ሁሉ፥ እግዚአብሔርም ሰውን ባበጀበት ወቅት ትልቅ ጥንቃቄ አድርጓል።

ሁለተኛ፥ እግዚአብሔር የሕይወት እስትንፋስ እፍ ስላለበት ሰው የተለየ ነው። ይህ ሥጋዊ ሕይወትን ብቻ የሚያመለክት አይደለም። እንስሳት ሕይወት ቢኖራቸውም፥ እግዚአብሔር የሕይወትን እስትንፋስ ሲሰጣቸው አንመለከትም። ይህ የእግዚአብሔር እስትንፋስ ልዩ ወደሆነው የሰው ክፍል ያመለክታል፤ ይኸውም መንፈሱ እግዚአብሔርን ይመስላል። ሰው የእግዚአብሔርን አምሳል የተቀበለው በእግዚአብሔር እስትንፋስ ነው። ስለሆነም የመንፈሳዊ መረዳት ግንኙነት የማድረግ (ንግግር)፥ ወዘተ. ብቃቱን ተቀብሏል። ይህ ሰውን ከእንስሳት በመለየት፥ በእግዚአብሔር ዓይኖች ፊት ትልቅ ዋጋ ያሰጠዋል።

6ኛ ጥያቄ፡- በዘፍ. 1 ስለ እግዚአብሔር አምሳል የተነጋገርነበትን ክልስ። ይህ አምሳል ምንን ያካትታል?

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ፥ ሌላው የእግዚአብሔር ስም ተጠቅሶ እናገኛለን። እግዚአብሔር እንዴት ‹ጌታ አምላክ› ተብሎ

እንደ ተጠራ ልብ በል። በዚህ ሥፍራ ጸሐፊው ሁለቱን የብሉይ ኪዳን አበይት የእግዚአብሔር ስሞች ያቀናጃቸዋል። የእግዚአብሔርን ገዥነትና ኃይል የሚያመለክተውን ኤሎሂም የተባለውን ስም ይጠቀማል። እንዲሁም ደግሞ ያህዌ ወይም ጄሆቫ የሚል ስም ይጠቀማል። ይህ አይሁዶች ከሁሉም በላይ በአክብሮት የሚመለከቱት የተለየ የእግዚአብሔር ስም ነበር። ጸሐፊው እዚህ ላይ ጄሆቫ የሚለውን ስም በመጠቀም፥ እግዚአብሔር ሰውን የሚወድና ከእርሱም ጋር ህብረት ለማድረግ የሚፈልግ የግል ባሕርይ የተላበሰ አምላክ የመሆኑን እውነታ እያመለከተ ነው። ቃል ኪዳን የገባው አምላክ ጄሆቫ ነው።

3. እግዚአብሔር ሰውን ያስቀመጠበት የተለየው የአትክልት ሥፍራ (2:8-14)።

እግዚአብሔር አዳምን የመፍጠሩን ሥራ ካጠናቀቀ በኋላ፥ በምድር ላይ የሚኖርበትን ልዩ ሥፍራ አዘጋጀለት። ሥፍራውም ‹ዔድን› በመባል ይታወቃል። ዔድን ማለት ‹ውብ ሥፍራ› ወይም ሁሉም መልካም የሆነበትና አንዳችም ክፉ ነገር የሌለበት ቆንጆ የአትክልት ሥፍራ ማለት ነው። እግዚአብሔር አዳም በጣም ደስተኛ እንዲሆን ፈልጎ ነበር።

ጸሐፊው ስለ ዔድን አንዳንድ ነገሮችን ይገልጻል፦

1. ዔድን ጸሐፊው ከነበረበት በስተምሥራቅ ነበረች። ይህም ማለት ጸሐፊው የመጀመሪያዋ ዔድን የት እንደ ነበረች ያውቅ ነበር ማለት ነው። ዔድን በመስፖታሚያ ሸለቆ፥ በዛሬዋ ኤራቅ ውስጥ የነበረች ይመስላል።

2. እግዚአብሔር ዔድንን ለሰው ልጅ የአትክልት ሥፍራ እንድትሆን በማዘጋጀት ትልቅ ጥንቃቄ አድርጓል። ዔድን ምናልባት ትልቅ አገር ላትሆን ትችላለች፤ ዳሩ ግን እግዚአብሔር ለአዳምና ሔዋን ያዘጋጃት የተለየ ውበትና ጥንቃቄ የሞላባት ሥፍራ ነች። በአትክልት ሥፍራው ውስጥ የተለያዩ ዓይነት ዛፎችን፥ በተለይም ፍሬ የሚሰጡትን፥ ሰዎች እየተመገቡዋቸው እንዲደሰቱ አደረገ። ዳሩ

ግን በአትክልት ሥፍራው ውስጥ እጅግ አስፈላጊዎቹ ነገሮች ሁለት ዛፎች ነበሩ። እነዚህ ዛፎች በኋላ በአዳምና ሔዋን ታሪክ ውስጥ ወሳኝ ሚና ተጫውተዋል፡-

ሀ) የሕይወት ዛፍ - ጸሐፊው ይህን ሲል ዛፍዋ ለሚመገቡዋት የዘላለም ሕይወት ተሰጣለች ማለት ነው። ስለ ሕይወት ዛፍ በታሪኩ ውስጥ ትንሽ ብቻ መገለጹ አስገራሚ ነው። አዳም የዚህችን ዛፍ ፍሬ ለመብላት አልተከለከለም ነበር። ኃጢአትን እስከሠራበት ጊዜ ድረስ የዚህችን ዛፍ ፍሬ በመብላት የዘላለም ሕይወት መንገድ ለእርሱ ክፍት ነበር። በኋላ ግን ሰው ከፍሬዋ ወስዶ እንዳይበላና በኃጢአቱም ለዘላለም እንዳይኖር፥ ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደው መንገድ በእግዚአብሔር ተዘጋ (3:22-24)። የራእይ መጽሐፍ በመንግሥተ ሰማያት ለመብላት ለሚፈልጉ ሁሉ በቂ ፍሬዎች ያሏት የሕይወት ዛፍ እንዳለች ይገልጻል (ራእይ 22:1-2)።

ለ. መልካሙንና ክፉን የምታስታውቅ ዛፍ- ለሰው የክፋት እውቀት የምታስገኝ ዛፍ ነበረች። ሰው ከዚህች ፍሬ እስከበላበት ጊዜ ድረስ፥ የሚያውቀው ነገር ቢኖር እግዚአብሔርን መታዘዝ ብቻ ነበር። የሥነ-መለኮት አዋቂዎች ይህንን ክፋት የማይታወቅበት (የጨዋነት) ዘመን ይሉታል። አዳም እዚአብሔርን የመታዘዝ ወይም ያለመታዘዝ ምርጫ እንደነበረው ቢያውቅም፥ በእውነቱ በመልካምና በክፉ መካከል ያለውን ልዩነት አያውቅም ነበር። አዳም ወደ ኃጢአት የሚገፋፋ የኃጢአት ተፈጥሮ አልነበረውም። በዚህም በምንኖርበት ዘመን ከምንኖረው ከእኛ የተለየ ነው። ሰው እንዳይበላ የተከለከለው ከዚህች ዛፍ ነበር። ይህችን ፍሬ መብላት ሞትን የሚያስከትለውን ኃጢአትና አለመታዘዝን ወደ ሰው ሕይወት አመጣ።

3. የዔድን ውበት በበርካታ ውኆች፥ በጌጣጌጦችና በወርቅ መኖር ተመልክቷል። በመካከለኛው ምሥራቅ፥ በጣም አነስተኛ ውኃ ብቻ ይገኛል። ስለዚህ፥ ብዙ ውኃ ማግኘት ታላቅ የብልጽግና ምልክት ነበር። በዔድን፥ ፍሬውን በሙሉ የሚያጠጣ ትልቅ ወንዝ ነበር።

ከሄድን ከወጣ በኋላ ወደ ፈሶን፡ ግዮን፡ ጤግሮስና ኤፍራጥስ፡ ለአራት ወንዞች ይከፈል ነበር።

ሀ) ፈሶን- ዛሬ የፈሶን ወንዝ ያለበትን ሥፍራ አናውቅም። ሆኖም በዛሬው ለሰው በማይታወቀው በኤውላጥ ምድር ውስጥ እንደሚገኝ ስለ ተገለጸ፡ በሙሴ ዘመን ይታወቅ ነበር ማለት ነው። የኤውላጥ ምድር በተጨማሪም በወርቁና በከበሩ ድንጋዮቹ ይታወቅ ነበር።

ለ) ግዮን- ግዮን ወደ ኩሽ ምድር ይገባ ነበር። አሁንም ሊቃውንት በዚህ ሥፍራ የተጠቀሰው ወንዝ የትኛውን እንደሚያመለክት አያውቁም። ጥንታዊው የኩሽ ክልል ከግብፅ በስተደቡብ የሚገኘው ሲሆን፥ ዛሬ የሱዳንና የኢትዮጵያ ሰሜናዊ ክፍል ተብሎ ይታወቃል። ዳሩ ግን ሊቃውንቱ ይህ ኩሽ በዚህ ሥፍራ የተጠቀሰው እንደሆነ አድርገው አይገምቱም።

እነዚህ ሁለቱም ወንዞች፥ ዛሬ ጤግሮስና ኤፍራጥስ ተብለው ከሚታወቁ ወንዞች አጠገብ ይፈስሱ የነበሩ ይመስላል።

ሐ) ጤግሮስ- በአሹር፥ ወይም በአሦር ምድር ውስጥ ነበር። በጥንት ጊዜ በጣም የታወቀ ወንዝ ነበር።

መ) ኤፍራጥስ የሚፈሰው ከጤግሮስ አቅራቢያ ሲሆን፥ እርሱም እንደዚህ የታወቀ ነበር።

7ኛ ጥያቄ፡- የጤግሮስንና የኤፍራጥስን ወንዞች አቅጣጫ ለማመልከት፥ ከመጽሐፉ በስተጀርባ ያለውን ካርታ ተመልከት።

እነዚህ ሁለቱም ወንዞች ዛሬ የታወቁ ናቸው። በኤራቅ ምድር ውስጥ ይፈስሳሉ። እነዚህ ወንዞች በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ጠቃሚ ሚና ተጫውተዋል። የተስፋዱቱ ምድር ሰሜናዊ ዳርቻዎች ተደርገው የተገለጹ ሲሆን፥ በኋላም የእስራኤል ሕዝብ በምርኮ የሚሰደደው ወደ እነዚህ ሁለት ወንዞች ክልል ነበር። በታሪክ እነዚህ ሁለቱ ወንዞች ለምለም ዳርቻ ወይም መሰፖታሚያን ይፈጥራሉ። ይህም ሥፍራ በሊቃውንት ዘንድ ሕይወት እንደተጀመረበት የሚታመኑበት ነው።

8ኛ ጥያቄ፡- ሙሴ ዔድንን በመዘርዘር የገለጸው ለምንድነው?

ጸሐፊው ዔድንን በዝርዝር የገለጸበት አቢይ ዓላማ፥ እግዚአብሔር ለአዳምና ሔዋን የነበረውን ፍቅርና እንዴት ውብ የሆነ የመኖሪያ ሥፍራ እንዳዘጋጀላቸው ለማሳየት ነበር። በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ለመሥራት የሚያነሳሳቸው ምንም ምክንያት አልነበራቸውም።

4. በዔድን ገነት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የነበረው ግንኙነት (2፡15-20)

እግዚአብሔር ለሰው መኖሪያነት በተለየ ሁኔታ ባዘጋጃት ውብ የአትክልት ሥፍራ ውስጥ፥ የመጀመሪያውን ሰው አዳምን አስቀመጠው። በዕብራይስጥ ቋንቋ «አዳም» ማለት «ሰው» ማለት ነው። ጸሐፊው በዚያ የአትክልት ሥፍራ ውስጥ ስለ አዳም ብዙ ነገሮችን ይናገራል።

ሀ) ሰው በዔድን ገነት ውስጥ የተቀመጠው ‹ያበጃትና ይጠብቃት ዘንድ› ነበር። ሰው በአትክልቱ ሥፍራ ውስጥ እንዲቀመጥ የተደረገው እጅና እግሩን አጣጥፎ እንዲዝናና አልነበረም። ኃላፊነትና ሥራ ተሰጥቶት ነበር። በኃጢአት ከመውደቁ በፊት እንኳ፥ ሰው መሥራት ነበረበት። ዳሩ ግን ያኔ አረሞች ወይም እሾሆች ስላልነበሩ፥ ሥራው አስቸጋሪ በመሆን ፈንታ አስደሳችና ትግልን የማይጠይቅ ነበር።

9ኛ ጥያቄ፡ - ሀ) እግዚአብሔር እንዲሠሩ ያዘዛቸው ለምን ይመስልሃል?

ለ) ይህ እግዚአብሔር በሥራ ላይ ስላለው አመለካከት ምን ያስተምረናል?

ሐ) ይህስ እኛ ብዙውን ጊዜ ስለ ሥራ ካለን አመለካከት የሚለየው እንዴት ነው?

ሰው በአትክልት ሥፍራው ውስጥ መሥራት ብቻ ሳይሆን፥ መንከባከብም ነበረበት። ለአትክልት ሥፍራው እንክብካቤ ስለማድረግ የተጠቀመበት ቃል ‹ማገልገል› የሚለውን ትርጉም ይሰጣል። የአትክልት ሥፍራው የእግዚአብሔር እንጂ፥ የአዳም አልነበረም። አዳም በምድር ላይ የፈለገውን ሁሉ የማድረግ መብት አልነበረውም።

ይልቁንም ዔድን ገነትን በመንከባከብ እግዚአብሔርን ማገልገል ነበረበት።

10ኛ ጥያቄ፡- ዘሌ. 25፡23 አንብብ።

ሀ) ጸሐፊው ምድሪቱ የማን እንደሆነች ይናገራል?

ለ) የእስራኤላውያን ከምድሪቱ ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት ምን መምሰል ነበረበት?

ሐ) በዙሪያችን ከሚገኙ ሰዎችና ከምንኖርባት ምድር ሊኖረን ስለሚገባው ግንኙነት የምንማራቸው አንዳንድ መመሪያዎች ምንድናቸው?

በእግዚአብሔር ፍጥረት ላይ ሥልጣን የተሰጠው ስለሆነ፥ የሰው ልጅ ኃላፊነት አለበት። ምድር እንደ ፈለግን የምንጫወትባት ንብረታችን እንዳልሆነች ሁል ጊዜም ማስታወስ አለብን። የእግዚአብሔር ንብረት ነች። የምንችለውን ሁሉ በማድረግ የመንከባከብ ኃላፊነት አለብን። ምድርን አለ አግባብ የመገልገልና የማጥፋት ማንኛውም አዝማሚያ ያለው ነገር ስሕተት ነው። ይህም ዛፎችን ሁሉ በመጨፍጨፍ ምድርን ምድረ በዳ-ማድረግ፥ ወይም በጣም ብዙ እንስሳትን በማሰማራት ምድርን ለመሸርሸር ማጋለጥ ሊሆን ይችላል። የሰው ልጅ ምድርን ለግል ጥቅምና እንደ ፈለገው የሚጫወትበት ነገር አድርጎ መመልከት ሲጀምር፥ እግዚአብሔር የፈጠረውን ነገር አውድሞት ያርፋል። እንስሳትም ለሰው ልጅ ቁጥጥር ተሰጥተዋል። ቢሆንም የእግዚአብሔር ንብረቶች ናቸው። ስለሆነም ሰው በእንስሳት ላይ የጭካኔ ተግባር ለመፈጸም፥ ወይም እነርሱን ለማጥፋት ሆን ብሎ የሚነሳሳበት መብት የለውም። የ‹ዕድገት› መሠረቱ የሚጣለው የሰው ልጅ ዓለምን ለመንከባከብና ለመጠበቅ ካለው ኃላፊነት ነው።

11ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ይህ ስለ ልማት ሥራ ዓላማ ምን ያስተምረናል?

ለ) ክርስቲያኖች ምድራቸውን በመንከባከቡ ረገድ ሊጫወቱ የሚገባቸው ሚና ምንድነው?

ሐ) ሰው የሚፈጽማቸውና ምድርን የሚያጠፉ አንዳንድ ነገሮች ምንድናቸው?

ለ. እግዚአብሔር ሰው በገነት ሲኖር እንዲጠብቀው አንድን ትዕዛዝ ሰጠው (2፡15-17)።

እግዚአብሔር ሰው የሚኖርበትን እጅግ የተሟላ ሁኔታ ፈጥሯል። ሰው በእግዚአብሔር ተባርኮ፥ በገነት ካለው ዛፍ ሁሉ የማናቸውንም ፍሬ ለመብላት ፈቃድ ትሰጥቶታል። አንድ የተከለከለው ነገር ብቻ ነበር። ሰው መልካምና ክፉ ከምታስታውቀው ዛፍ ፍሬ እንዲበላ አልተፈቀደለትም ነበር። እንዳይበሉ ከሚከለክለው ትዕዛዝ ጋር፥ በልተው ቢገኙ የሚከተላቸው የቅጣት ማስጠንቀቂያም ተሰጣቸው። ፍሬውን ቢበላ እንደሚሞት፥ እግዚአብሔር አዳምን አስጠነቀቀው።

12ኛ ጥያቄ፡- ሀ) እግዚአብሔር ይህን ትዕዛዝ ለምን ለአዳም ሰጠው?

ለ) እግዚአብሔር ይህችን ዛፍ በገነት ያስቀመጠው ለምድነው?

ብዙ ሰዎች ለምን እግዚአብሔር መልካምና ክፉ የምታሳውቀውን ዛፍ ከአዳም ፊት አስቀምጦ ከፍሬዋ እንዳይበላ እንደከለከለው ይደነቃሉ። ይህን በማድረጉም፥ ለአዳምና ሔዋን መውደቅ ጥፋተኞቹ ወዳቂዎቹ ሳይሆኑ እግዚአብሔር ነው ለማለት ይፈልጋሉ።

ምንም እንኳ እግዚአብሔር ይህን ያደረገባቸውን ምክንያቶች ባናውቅም፥ የሚከተሉትን ነገሮች ግን አሳምረን እናውቃለን፡-

1. ፈጣሪ፥ የፍጥረት ንጉሥ እንደመሆኑ መጠን፥ እግዚአብሔር የፈለገውን ነገር የማድረግ መብት አለው። በገነት ውስጥ መልካምና ክፉ የምታሳውቀውን ዛፍ የማስቀመጥ መብት ነበረው። ስለዚህ እግዚአብሔርን በድሏል ብሎ መውቀስ ትክክል አይደለም። ይህን ካደረግን ግን፥ እግዚአብሔርን በሕይወታችን በንጉሥነቱና በፈጣሪነቱ ከሚግባው ዙፋን ላይ ለመፈንቀል እየሞከርን ነው ማለት ነው።

2. እግዚአብሔር አፍቃሪ አምላክ ነው። እግዚአብሔር ዛፍዋን በገነት ውስጥ ያስቀመጠው የሰውን ልጅ ለመጣል ብሎ አልነበረም። እግዚአብሔር በአምሳሉ በፈጠረው ሰው መሞት ደስ አይሰኝም። እግዚአብሔር ለሰው በተለይ ያዘጋጃትን ውብ ሥፍራና እንዲበላም

የሰጠውን በርካታ ነገሮች በመመልከት፡ በሰው ላይ የነበረውን ፍቅር የተሞላ እንክብካቤ ለመረዳት እንችላለን።

3. ምናልባት የእግዚአብሔር ዓላማ፥ ሰው ለእግዚአብሔር ያለውን ፍቅር በመታዘዝ እንዲገልጽ ለማስቻል ነበር።

13ኛ ጥያቄ፡- ለኢየሱስ ያለንን ፍቅር እንዴት እንገልጻለን? (ዮሐ. 14፡15 ተመልከት)።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር የምንገልጽበት የመጀመሪያ መንገድ፥ ትዕዛዛቱን በማክበር ነው። እግዚአብሔር ለአዳም እርሱን ለመታዘዝ ከባድ ቀንበር አልጫነበትም። ከፍሬያቸው ለመብላት በርካታ ዓይነት ዛፎች ነበሩ። አንዲት ዛፍ ብቻ ነች የተከለከለችው። ይሁንና አዳም ከፍሬዋ የማይበላውን አንዲት ዛፍ ብቻ በማስቀረት፥ እግዚአብሔር አዳም ትዕዛዙን በማክበር ፍቅሩን በተግባር እንዲያረጋግጥ ሁሉንም አመቻችለት። ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተደጋግሞ የምናገኘው መመሪያ ነው። የእግዚአብሔር ሰዎች ለእግዚአብሔር ያላቸውን ፍቅር የሚያሳዩበት መንገድ ሁል ጊዜም በመታዘዝ ነው። እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ለመታዘዝ ወይም ላለመታዘዝ መምረጥ ከሚችሉበት ኃይል ጋር ባይፈጥራቸው ኖሮ፥ ለእግዚአብሔር ፍቅራቸውን የሚገልጹበት ብቃት አይኖራቸውም ነበር። ለመምረጥ መቻልና በምርጫቸውም መዘዝ መከራን መቀበል፥ ሰዎች ከእንስሳት የሚለዩበት አንዱ ታላቅ ነጥብ ነው።

እዚህ ላይ የተጠቀሰ ሌላም መመሪያ ያጋጥመናል። ይኸውም አለመታዘዝና ኃጢአት ቅጣትን እንደሚያስከትል ነው። ሰው እግዚአብሔርን በማይታዘዝበት ጊዜ ሁሉ ሞት የማይቀርለት ቅጣት ይሆናል።

‹ሞት› የሚለው ቃል ውስጥ ቁልፍ አሳብ ‹የሕወት ማብቃት› አይደለም። ይልቁንም ሞት ማለት ‹መለየት› ማለት ነው። ሥጋዊ ሞት የሰው መንፈስ ከሥጋው መለየት ነው። መንፈስ ግን መኖሩን ይቀጥላል። መንፈሳዊ ሞት፥ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን ህብረት መለየቱ ነው። አዳምና ሔዋን ኃጢአትን ባደረጉ ጊዜ በመጀመሪያ መንፈሳዊ ሞት፥ ኋላም ሥጋዊ ሞት አግኝታቸዋል።

ሐ. እግዚአብሔር አዳምን ስም እንዲያወጣላቸው በመጠየቅ በእንስሳት ላይ ያለውን የበላይነት አመልክቷል (2፡18-20)።

በዘፍ. 1፡28 እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን በፈጠራቸው ፍጥረታት ላይ እንዲገዙ ነግሮአቸዋል። ካለፈው ሳምንት ትምህርት እንደምታስታውሰው፥ አንድን ነገር ለ‹መሰየም› መቻል፥ ሰያሚው በዚያ ነገር ላይ ያለውን ሥልጣን የሚያመለክት የዕብራውያን ባሕል ነው። በፍጥረት መጀመሪያ እግዚአብሔር ቀንና ሌሊት፥ ሰማይ፥ ምድርና፥ ውኆችን በመሰየም በፍጥረቱ ላይ ያለውን ሥልጣን አሳይቷል። ለሰውም እንስሳትን የመሰየም ሥልጣን ሰጠው። እግዚአብሔር እንስሳትን ወደ አዳም አመጣና አዳም ስም አወጣላቸው። የነገሥታት ንጉሥ በሆነው በእግዚአብሔር አገዛዝ ሥር፥ ሰው ምድራዊ ንጉሥ በመሆን ይገዛ ጀመር።

ዳሩ ግን አዳም እንስሳቱን ሲሰይም ሳለ፥ አንድ ነገር እንደተገነዘበ ጥርጥር የለውም። እግዚአብሔር የፈጠራቸው እንስሳት ሁሉ ጥንድ ነበሩ- ተባእትና እንስት። ከተመሳሳይ ዝርያ ውስጥ ተባእትና እንስት እንደመሆናቸው፥ ብቸኞች አልነበሩም። ዳሩ ግን በምድር ላይ እርሱን የሚመስል ስላልነበር፥ ሰው ብቸኛ ነበር።

እግዚአብሔር አዳምን ከፈጠረ በኋላ፥ ብቸኛ መሆኑን ተገነዘበ። በፍጥረት ሁሉ ውስጥ እግዚአብሔር ‹መልካም አይደለም› ያለው አንድ ነገር ብቻ ነበር። እግዚአብሔር ሌሎች ነገሮችን ሁሉ ‹መልካም› እንደሆኑ ተናግሯል። አዳም ብቸኛ መሆኑ ግን ‹መልካም አልነበረም›። እግዚአብሔር ሴትን ስለ መሥራቱ ሁለት ምክንያቶችን ይሰጣል። በመጀመሪያ፥ ረዳት መሆን ነበረባት። ሁለተኛ፥ ‹የምትመች ጓደኛ› መሆን ነበረባት። እንደወንድየው ያለ ተፈጥሮ ሊኖራት ይገባ ነበር። በእዚህ ዓይነት በዕውቀትና በመንፈስ እንደእርሱ በመሆን፥ ከአዳም ጋር በሁሉም ነገር እውነተኛ ተካፋይ መሆን ነበረባት። እውነተኛ ጓደኝነትም ሊኖር ይገባ ነበር። ስለሆነም ሴቷ በእግዚአብሔርም በወንድም አምሳል ተፈጥራለች። ያለ ሔዋን፥ አዳም እግዚአብሔር እንዲሆን የሚፈልገውን ሁሉ ለመሆን አይችልም ነበር። አዳምና ሔዋን ሁለቱም ሙሉ ለመሆን አንዳቸው ሌላውን ይሻሉ።

14ኛ ጥያቄ፡- ይህ ባልና ሚስት ሊኖራቸው ስለሚገባው ግንኙነት ምን ያስተምረናል?

5. አዳምን ለመርዳት የሔዋን መፈጠር (2:20-25)

በጥንቱ ዓለም ሃይማኖቶች፥ ስለ ሴት አፈጣጠር የተነገረው በጣም ትንሽ ነው። በዘፍጥረት ውስጥ ግን ስለ ሔዋን አፈጣጠር ግሩም ታሪክ እናገኛለን። በእዚህ ውስጥ እግዚአብሔር ለጋብቻ የነደፈውን ትልም እንመለከታለን።

15ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ሔዋን የአዳም ረዳት መሆን ነበረባት ሲል ምን ማለት ነው?

ለ) ይህ ዛሬ በባልና በሚስት መካከል ስላለው ግንኙነት ምን ያሳያል?

እግዚአብሔር ወደ አዳም በተመለከተ ጊዜ፥ አዳም ጓደኛ፥ ‹ረዳት› እንደሚፈልግ ተገነዘበ። ብዙዎች ረዳት የሚለውን ቃል የበታችነትን የሚያመለክት አድርገው ይወስዳሉ። ይህ ማለት ወንድ በሥልጣን ከሴት በላይ ነው ብለው ይረዳሉ። የሴት ሚና እንደ ጓደኛ በእኩልነት ሳይሆን፥ እንደባሪያ ለወንድ ማገልገል ነው ይላሉ።

ዳሩ ግን ‹ረዳት› የሚለው ቃል፥ የሚጎድለውን የሚያሟላ፥ ሰው በራሱ ለማድረግ የማይችለውን ነገር ለማከናወን የሚረዳ ማለት ነው። ይኸው ተመሳሳይ ቃል ስለ እግዚአብሔርም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ጊዜ ተጠቅሷል (ዘጸ. 18:4 ተመልከት)። የሔዋን የረዳትነት ሚና በሥራው እየተካፈለች፥ እርሱ ብቻውን ለማከናወን በማይችላቸው ነገሮች እየረዳች፥ ከአዳም ጎን ሆና መሥራት ነበር።

እግዚአብሔር ወንድን ከምድር አፈር ሲሠራ፥ ሴትን ደግሞ ከወንድ ሠራት። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው፥ እግዚአብሔር ከአዳም ጎን አንዲት አጥንት፥ ምናልባትም የጎድን አጥንት ወስዶ ሴትን ፈጥሯል። አንድ ጠቢብ እንደተናገረው ሁሉ፥ በወንድ ላይ ገዥ እንዳትሆን እግዚአብሔር ሴትን ከወንድ ራስ ላይ አልፈጠረም፤ የወንድ ተገዢ እንዳትሆን ከወንድ እግር አልፈጠረም፤ ነገር ግን አብረው በእኩልነት እግዚአብሔርን እንዲያገልግሉ ከወንድ ጎን ፈጥሯታል። በታሪኩ ውስጥ

አዳም ከሔዋን ስለ መብለጡ የተሰጠ ፍንጭ የለም። ሁለቱም እኩል ነበሩ። ሁለቱም የእግዚአብሔር አምሳል ነበራቸው። በጋራ፥ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ያዘጋጀውን እቅድ መፈጸምና ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ማቅረብ ነበረባቸው።

16ኛ ጥያቄ፡ - ከእዚህ ስለ ጋብቻ ምን እንማራለን?

ከሔዋን መፈጠር በኋላ፥ ለመጀመሪያ ጊዜ የአዳምን ንግግር እንሰማለን። ቃላቱም እግዚአብሔር ለእርሱ በተለየ ሁኔታ ሴትን በመፍጠሩ የተሰማውን ደስታ የገለጸባቸው ነበሩ። ‹ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት፥ ሥጋም ከሥጋዬ ናት› የሚሉት ቃላት አንድነትንና እኩልነትን ያመለክታሉ።

ከሔዋን አፈጣጠር ውስጥ፥ ሙሴ ስለ ጋብቻ ትልቅ ትምህርት አግኝቷል። በመጀመሪያ፥ የባልና ሚስት የመጀመሪያ ታማኝነታቸው ለቤተሰቦቻቸው ሳይሆን፥ እርስ በእርሳቸው እንደሆነ ተናግሯል። ባል ቤተሰቦቹን ትቶ ከሚስቱ ጋር መተባበር ነበረበት።

17ኛ ጥያቄ፡ - ሀ) በቀድሞው የኢትዮጵያውያን ባሕል፥ ብዙውን ጊዜ አዲስ ባልና ሚስት ለመኖር የሚሄዱት ወደማንኛው ቤት ነበር?

ለ) የበለጠ ትብብር ያለው፥ ከባል ቤተሰብ ጋር ነው ወይስ ከሚስት?

በዕብራውያን ባሕል፥ ብዙውን ጊዜ ሚስት ወደ ባልዋ ቤተሰቦች ዘንድ ትመጣና አብራው ትኖር ነበር። ይህንንም በኋላ ላይ ርብቃ ወደ አብርሃም ቤት በመምጣት ከይስሐቅ ጋር ስትኖር እንመለከታለን። ዳሩ ግን ሙሴ የባልና ሚስት ትስስር ወንድ ልጅ ወይም ሴት ልጅ ከቤተሰባቸው ጋር ከሚኖራቸው ትስስር የጠነከረ መሆን እንዳለበት ተናግሯል።

ሁለተኛ፥ ባልና ሚስት ‹አንድ ሥጋ› መሆን ነበረባቸው። ይህ በቀዳሚ ሁኔታ በግብረ-ሥጋ ግንኙነት አንድ መሆንን አያመለክትም። ይልቁንም በመተባበር አንድ መሆንን ያመለክታል። ዓላማቸው አንድ መሆን አለበት። በህብረት መሥራት አለባቸው። መንፈሳቸው የተባበረ

መሆን አለበት። ከማንም በላይ የባል የቅርብ ወዳጅ ሚስት፥ የሚስት የቅርብ ወዳጅ ባል መሆን አለበት።

18ኛ ጥያቄ፡- ይህ በኢትዮጵያውያን ጋብቻ ውስጥ ምን ያህል እውነት ነው? ለምን?

ሦስተኛ፥ ዘፍጥረት 2 ቀላል በሚመስል ዓረፍተ ነገር ይፈጸማል- ‹አዳምና ሚስቱ ሁለቱም ዕራቁታቸውን ነበሩ፤ አይተፋፈሩም ነበር›። ይህ ልብስ አይለብሱም ነበር ማለት ብቻ አይደለም። በእዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ሁለት እውነቶች አሉ፡- በመጀመሪያ፥ አዳምና ሔዋን እርስ በእርሳቸው በጣም ግልጽ ነበሩ። አንዳቸው ከሌላቸው ምንም ነገር ለመደበቅ አይሞክሩም ነበር። ግልጽና ታማኝ ነበሩ። አንዱ የሌላውን አሳቦች፥ እቅዶች፥ መሻቶች፥ ዓላማዎች፥ ወዘተ. ያውቅ ነበር።

ሁለተኛ፥ ምንም ዓይነት ክፋት የማያውቁ ንጹሐን ነበሩ። አዳምና ሔዋን ኃጢአት በሠሩ ጊዜ በመጀመሪያ የተፈጸመው ነገር ዕራቁትነታቸውን ማወቃቸው ነበር። ንጽሕናቸውን አጡ። ከውድቀቱ በፊት፥ ሰው ምንም ክፋት አያውቅም ነበር። እግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉ መልካምና ያማረ ነበር።

19ኛ ጥያቄ፡- ከእነዚህ ጥቅሶች ስለ እግዚአብሔር የጋብቻ ቅንጅት የምንማራቸውን ነገሮች ዘርዝር።

እግዚአብሔር ስላቀናጀው ጋብቻ የምንማራቸውን ነገሮች በአጭሩ እንዘረዝራለን። የማናችንም ጋብቻ ቢሆን እግዚአብሔር ካቀደው ጋር ሙሉ ለሙሉ አይገጥምም። ዳሩ ግን ከየትኛውም ባሕል ብንመጣም፥ እግዚአብሔር የጋብቻ ግንኙነቶቻችንን ከእርሱ ዓላማና እቅድ ጋር ለማስተካከል እንድንሻ ይፈልጋል።

1. ሴት ለወንድ ወንድም ለሴት ተፈጥረዋል። በሥጋና በመንፈስ ጤናማ ለመሆን አንዳቸው ለሌላቸው አስፈላጊዎች ናቸው።

2. ለሰው የተፈቀደው ብቸኛው የግብረ-ሥጋ ግንኙነት የተቃራኒ ፆታዎች ነው። ይህ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ትልቅ ችግር ላይሆን ቢችልም፥ በበርካታ የዓለም አገሮች ወንድ ከወንድ እና ሴት ከሴት ጋር የሚፈጽሙት የግብረ-ሰዶም ግንኙነት የተፈቀደ ነው።

ይህ በእግዚአብሔር ዓይኖች ፊት የከፋ ኃጢአት ነው (ሮሜ 1:27)።

3. በመጀመሪያው ጋብቻ ውስጥ፥ አንዱ በሌላው ላይ ገዥ ለመሆን ወይም ሌላው ለሌላው ተገዥ ለመሆን አላስፈለገውም ነበር። ሁለቱም ፍጹም እኩል ነበሩ። ይህም ሊሆን የቻለው የኃጢአት ተፈጥሮ ስላልነበራቸው ነው። ለወንድ የበላይነት የተሰጠውና ሴትም ታዛዥ እንድትሆን የተደረገው ከውድቀት በኋላ ብቻ ነው። በውድቀት ጊዜ፥ መጀመሪያ በመፈጠሩ ለወንድ የበላይነት ተሰጠው (1ኛ ጢሞ. 2:11-14)። ዳሩ ግን ይህ የበላይነት አምባገነናዊ ግንኙነት ሳይሆን፥ በፍቅር መምራት ማለት ነው። በአዲስ ኪዳን ውስጥ፥ ወንድና ሴት እርስ በእርሳቸው ተገዢ እንዲሆኑ መነገር ብቻ ሳይሆን፥ ወንዱ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን የወደዳትን ያህል ሴቷን የመውደድ ከባድ ኃላፊነት ተሰጥቶታል (ኤፌ. 5:28-33)።

20ኛ ጥያቄ፡- ወንድየው በጋብቻ ውስጥ ይህን እንዴት ማሳየት እንደሚችል ምሳሌዎችን ስጥ።

4. የጋብቻ ግንኙነት ከሌሎች ሰብዓዊ ግንኙነቶች ሁሉ ቀደምትነት ይኖረዋል፤ ከወዳጆቻችን ጋር ከሚኖረን ግንኙነት በላይ አስፈላጊ ነው። እንዲያውም ከቤተሰቦቻችን ጋር ከሚኖረን ግንኙነትም በላይ አስፈላጊ ነው። ከእዚህ በላይ አስፈላጊ የሚሆነው ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ብቻ ነው።

5. በባልና ሚስት መካከል ፍጹም ታማኝነትና ግልጽነት መኖር አለበት። አንድ ዓይነት እቅዶችን፥ መሻቶችንና፥ መንፈሳዊ ዓላማዎችን አንግበው መሥራት አለባቸው። የግል እቅዶቻቸውን አስወግደው በጋራ እንደ አንድ ቡድን መሥራት ይገባቸዋል። አንድ ሥጋ ናቸው። ሆኖም ሁላችንም እራስ ወዳዶችና በመጀመሪያ ደረጃ የእራሳችንን መንገዶች ስለምንከተል፥ ይህን መፈጸም በጣም ከባድ ይሆናል።

6. ጋብቻ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል መፈጸም አለበት። እግዚአብሔር ለአዳም ብዙ ሔዋኖችን አልፈጠረም፤ ወይም ለሔዋን ብዙ አዳሞችን አልፈጠረም። በጋብቻ ውስጥ

የእግዚአብሔር እቅድ አንድ-ለአንድ (ሞኖጌሚ) ነው። ምንም እንኳ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ውስጥ ብዙ ማግባትን (ፖሊጌሚ) ቢታገሥም፥ ምርጫው ሁል ጊዜም አንድ-ለአንድ ነው።

21ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በአንተ ቤተ ክርስቲያን አንዳንድ ሰዎች ከአንድ ሚስት በላይ በማግባታቸው የተፈጠሩ ችግሮች ነበሩ?

ለ) ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ዓይነት አጋጣሚዎችን እንዴት ትመለከታለች?

ሐ) ከአንድ በላይ ሚስቶች ባሉባቸው ቤተሰቦች ውስጥ የሚነሱ ተጨማሪ ችግሮች ምንድናቸው?

7. በጋብቻ ውስጥ ፍጹም ታማኝነት መኖር አለበት። በእግዚአብሔር ዓይኖች ፊት ባልና ሚስት አንድ ሥጋ እንደሚሆኑ ሁሉ፥ በመንፈሳዊም ሆነ በሥጋዊ ነገር አንድ መሆን አለባቸው። ይህም ማለት ወንዱም ሆነ ሴቷ ከጋብቻ በፊትም ሆነ በኋላ ባለቤቱ ካልሆነ ሰው ጋር የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ሊፈጽሙ አይችሉም ማለት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ጊዜ ከተኮነኑት ኃጢአቶች አንዱ ይህ ነው።

22ኛ ጥያቄ፡- ብዙ ክርስቲያኖች ከማግባታቸው በፊት ወይም በኋላ ይህን መመሪያ የሚጥሱት እንዴት ነው?

8. ሴት ‹ረዳት› እንጂ አገልጋይ ወይም ባሪያ አይደለችም። ሴት የወንድ ንብረት የምትሆን ዕቃ አይደለችም። ይልቁንም ባልና ሚስት እግዚአብሔር እንዲሆኑለት የሚፈልገውን ሆነው ለመገኘት በደስታና በሓዘን ጊዜያት እርስ በእርሳቸው ሊረዳዱ ይገባል።

23ኛ ጥያቄ፡- ከእነዚህ መመሪያዎች በጋብቻህ ውስጥ ለመከተል እጅግ የሚከብዱህ የትኞቹ ናቸው? ለምን?

እንደ እግዚአብሔር ዕቅድ ቢሆን ጋብቻ እንዴት ባማረ ነበርን የሚያሳዝነው ግን ኃጢአት ወደ ዓለም እንደገባ የተበላሸው የመጀመሪያው ነገር በባልና ሚስት መካከል የነበረው ህብረት ነው። ክርስቲያኖች እንደመሆናችን፥ በጋብቻ ውስጥ ወደ ነበረው የእግዚአብሔር አሳብ ለመመለስና ለተቀረው ዓለም ምሳሌዎች ለመሆን መሻት አልብን። ግን ይህን እያደረግን ነውን?

ሁለተኛ ቀን፡- ዘፍጥረት 3፡1-7

እግዚአብሔር የመጀመሪያዎቹ ወንድና ሴት የሚኖሩበትን ፍጹም ያማረ ሁኔታ አዘጋጀ። የሚበሉት በቂ ምግብ ነበር። በወንዱና በሴቲቱ እንዲሁም በእነርሱና በአምላካቸው መካከል ፍጹም የሆነ ህብረት ነበር። ሰውን በአምላኩ ላይ እንዲያምፅ የሚፈትነው ኃጢአት በዓለም ላይ አለነበረም። እንዲሁም ፈተናን ወደ ሕይወታችው የሚጋብዝ የኃጢአት ተፈጥሮም አልነበራቸውም። ሁሉም ፍጹም ሰላምና ህብረት ነበራቸው። የሚያሳዝነው ግን ታሪኩ በዚህ አላበቃም። በዘፍ. 3-5 ራሱን የቻለ አንድ ክፍል ነው። ከዚህ የሚቀጥሉት ምዕራፎች ሁሉ ሰው በኃጢአት ውስጥ ከመውደቁ የተነሣ የተከሰቱትን ሁኔታዎች ይመለከታሉ።

24ኛ ጥያቄ፡- ዘፍ. 3-5 አንብብ። በእነዚህ ክፍሎች፥ ከኃጢአት የተነሣ የተከሰቱትን ሁኔታዎች ዘርዝር።

25ኛ ጥያቄ፡- እንደገና ዘፍ. 3፡1-7 አንብብ።

ሀ) እባብ የተገለጸው እንዴት ነው?

ለ) የእባቡ የመጀመሪያ ጥያቄ ዓላማ ምን ይመስልሀል?

ሐ) የሔዋንን ምላሽ፥ በ2፡16-17 ከተገለጸው የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ጋር አወዳድር። ሔዋን በመጀመሪያው ትዕዛዝ ላይ የጨመረችው ምንድነው?

መ) ሔዋን ለጥያቄው ለሰጠችው መልስ፥ እባቡ ምን ምላሽ ሰጠ?

ሠ) የእባቡ መልስ በእግዚአብሔር ባሕርይና ዓላማ ላይ ጥርጣሬ የሚፈጥረው እንዴት ነው?

ረ) እግዚአብሔርን ባልታዘዙ ጊዜ፥ በመጀመሪያ አዳምና ሔዋን ያገኙት ውጤት ምን ነበር?

ሰ) ዓይኖቻቸው ተከፈቱ ማለት ምን ማለት ነው?

ሸ) ጸሐፊው ዕራቁታቸውን እንደሆኑና እንደፈሩ የገለጸው ለምንድነው? (ዕራቁት ስለመሆን የትናንትናውን ትምህርት ተመልከት)።

26ኛ ጥያቄ፡- የአዳምና ሔዋንን ውድቀት ከ ዮሐ. 2፡15-17 እና ያዕ. 1፡13-15 አወዳድር።

ሀ) በ1ኛ ዮሐንስና በያዕቆብ ውስጥ የሚገኙት ጥቅሶች በዘፍጥረት 3፡1-7 ታሪክ ውስጥ የታዩት እንዴት ነው?

ለ) አዳምና ሔዋን በኃጢአት የወደቁበትን ሁኔታ እኛ ከወደቅንበት ጋር አወዳድር።

ሐ) ያሉት አንዳንድ ልዩነቶችና ተመሳሳይነቶች ምንድናቸው?

በዛሬው ትምህርታችን፥ የመጀመሪያውን ፈተናና የሰውን በኃጢአት መውደቅ እንመለከታለን። ጸሐፊው ኃጢአት ከየት እንደመጣ እያሳየን ብቻ አይደለም፤ ዳሩ ግን ፈተናን ተረድተን ከኃጢአት እንድንሸሽ፥ እንዴት ፈተና ወደ ኃጢአት ሊመራ እንደሚችል ሊያስተምረን ይሻል። እንዲሁም ኃጢአት ሁሉ በእግዚአብሔር ወደ መቀጣት እንደሚያመራ እንመለከታለን። የፈተናና የኃጢአት ሁሉ እምብርቱ ለእግዚአብሔር ትዕዛዛት አለመታዘዝና የራሳችንን ሕይወት ለመምራት ያለን ፍላጎት ነው።

አዳምና ሔዋን ፍጹም በተለየ ሁኔታ በዔድን ገነት ውስጥ ለምን ያህል ጊዜ እንደኖሩ አናውቅም። አንድ ቀን፥ አንድ ወር፥ አንድ ዓመት ነውን? እግዚአብሔርና ሰው የቀኑ ሙቀት አሽቆልቁሎ የምሽቱ ቀዝቃዛ አየር ሲነፍስ የመገናኘት ልማድ እስኪኖራችው ድረስ ቆይተው ነበር። ዳሩ ግን አዳምና ሔዋን ልጅ ስላልወለዱ በጣም ብዙ ጊዜ ሊሆን አይችልም።

ከዕለታት አንድ ቀን ያ ፍጹም የነበረው የገነት ሰላም ደፈረሰ። በመጀመሪያ፥ ፈተናው ንጹሕ ይመስል ነበር። በእባብ መልክ ተከሰተ። የዘፍጥረት ጸሐፊ ይህንን እባብ ተንኮለኛና ውብ እንደሆነ አድርጎ ብቻ ይገልጸዋል። ጸሐፊው እባቡ ማን እንደሆነ ለመግለጽ አልሞከረም፤ ይልቁንም ሔዋንን ወደ ኃጢአት በመሩት ቃሎቹ ላይ ያተኩራል። ዳሩ ግን የሚከተሉትን ነገሮች ስለ እባቡ ልንረዳ እንችላለን፥

1. እባቡ ከሌሎች የዱር እንስሳት ጋር ስለተወዳደረ፥ እግዚአብሔር ከፈጠራቸው አራዊት አንዱ ነበር። የእግዚአብሔር ፍጥረት አካል እንደመሆኑም፥ እንደሌላው ሁሉ መልካም ተብሏል።

2. እባቡ ትንኮለኛ ነበር። ትንኮለኛ የሚለው ቃል በዕብራይስጥ ሁለት ትርጉሞች ሊኖሩት ይችላል - መልካምና ክፉ። ሰውን በማታለል ክፉ ነገር ለመሥራት የሚመራ መሠሪ ማለት ሊሆን ይችላል። እንዲሁም ደግሞ ወጥመዶች ወይም አደጋ የሚያስከትሉ ነገሮች ያሉበትን ሥፍራ በመረዳት በጥንቃቄ የማለፍንም መልካም አሳብ ሊይዝ ይችላል (ምሳሌ 14:15፥ 18፤ 22:3)።

3. ምናልባት ዛሬ በጋኔን በተያዙት ሰዎች ውስጥ እንደሚገባ ሁሉ፥ ሰይጣን በእባቡ ውስጥ ገብቶ ይሆናል። እንደእግዚአብሔር ሁሉ ሰይጣንም መንፈስ ስለሆነ፥ ሥጋዊ አካል የለውም። ስለዚህም እንደሰው፥ ወይም እባብ ሥጋዊ አካል ባላቸው ፍጥረታት ውስጥ ይገባል። ለሰው እንዳይታወቅም በእባብ ውስጥ ተሸፍኖ መጣ። እባቡ በኋላ ላይ ስለ ተረገመ ከሰይጣን ጋር የተባበረ ይመስላል። በኋላ ሰይጣን የቀድሞው እባብ ተብሏል (ራእይ 12:9)።

ለመጀመሪያ ጊዜ በእግዚአብሔር መልካም ፍጥረት ውስጥ የክፉን ሕልውና እንመለከታለን። ሰይጣን መቼ እንዳመፀና እንደተጣለ አናውቅም። በኢሳ. 14:12-15 እና ሕዝ. 28:11-17 ሰይጣን በአንድ ወቅት ‹የአጥቢያ ኮከብ› ተብሎ በመጠራቱ ከእግዚአብሔር መላእክት ሁሉ በላይ የነበረ ይመስላል። ዳሩ ግን ትዕቢቱና እንደእግዚአብሔር የመሆን መሻቱ ወደ ኃጢአት መራው። ከሰማይ ተጣለ። ከዚያም የእግዚአብሔር ታላቁ ጠላት በመሆን፥ እግዚአብሔር የፈጠራቸውን መልካም ነገሮች ሁሉ ማጥፋትንና ከእግዚአብሔር መንግሥት በተቃራኒ የእራሱን መንግሥት መመሥረትን የዘመኑ ሁሉ ትግል አድርጎ ጀመረ። የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ በክፉና በመልካም ወይም በሰይጣንና በእግዚአብሔር መካከል የሚደረግ የጦርነት ታሪክ ሊባል ይችላል። አዳምና ሔዋንን ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን ሕብረት ለማጥፋት ሠይጣን ሔዋንን ተፈታተናት።

27ኛ ጥያቄ፡- ይህ ጦርነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የታየው እንዴት ነው?

የእግዚአብሔር ቃላት ሕይወትን ሲያመጡ፥ የሰይጣን ቃላት እንዴት ውዥንብርንና ሞትን እንዳስከተሉ እንመለከታለን። ሰይጣን የእግዚአብሔርን ቃላት የእርሱን ዓላማ በሚያሳካ መንገድ በመለወጥ ሥራውን ጀመረ። አብዛኛዎቹ የሐሰት ትምህርቶች የሚጀምሩት መልካሙን ከክፉ ጋር በመቀየጥና የእግዚአብሔርን እውነት በውሸት በመበከል ነው።

1. የፈታኙ ጥያቄ (ቁጥር 1)

ምናልባት ሔዋንን በመጀመሪያ የሳባት እባቡ እየተናገረ ስለ ነበረ ይሆናል። ፈተና ሁል ጊዜም የሚጀምረው መልካም በሚመስል ነገር ነው። ክፉ ውጤቶች ድብቅ ናቸው። «በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዝዞአልን?» የሚለው የመጀመሪያ ጥያቄ ንጹሕ ይመስላል። ሰይጣን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ወዲያውኑ አልካደም ነበር። ይልቁንም በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ላይ የጥርጣሬ ጥላ ለማሳረፍና ሴቲቱ በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ላይ ያላትን ዕውቀት ለመፈተን፥ ጥንቃቄ የተሞላበትን ጥያቄ አቀረበ። ከሰይጣንና ከፈተናው ሮጣ እንደማምለጥ፥ ሔዋን እርሱን በመስማትና ምላሽ በመስጠት፥ በፈተና የምትወድቅበትን በር ከፈተች። ፈተና በእራሱ ኃጢአት ባይሆንም፥ ድል ካልነሱት ወደ ኃጢአት ይመራል።

2. የሔዋን መልስ (ቁጥር 2-3)

የሔዋንን መልስ በምንመለከትበት ጊዜ፥ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ታውቅ እንደነበረ እንረዳለን። መልካምና ክፉ ከምታስታውቀው ዛፍ በስተቀር፥ ከሌሎች ዛፎች ሁሉ ፍሬዎችን መብላት እንደምትችል ታውቅ ነበር። ዳሩ ግን በአንድ በሆነ ምክንያት ሔዋን በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ላይ የማሻሻያ አሳብ ጨመረች። ከመጀመሪያው ትዕዛዙ ጋር በማይመሰል መልኩ፥ ‹እንዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ፤ አትንኩትም› ብሎናል አለች። ሔዋን በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ላይ ለምን ጨምራ እንደተናገረች አናውቅም። ምናልባት እግዚአብሔርን እንደምትታዘዝ ለማረጋገጥና ለዚሁም መታዘዝ የሚረዱአትን ተጨማሪ ትዕዛዞች

ለመፍጠር ፈልጋ ይሆናል። ዳሩ ግን እርስዋ የጠቀሰችው ትዕዛዝ የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ትክክለኛ ቅጂ አካል አልነበረም። ይህም ጭማሪ፥ ለሰይጣን ወደ ኃጢአት እንዲመራት መንገድ ከፍቶለታል።

አንዳንድ ሰዎች ሰይጣን ወደ አዳም ሳይሆን ወደ ሔዋን የቀረበው፥ እግዚአብሔር በመጀመሪያ ትዕዛዙን ለሔዋን ሳይሆን ለአዳም ስለ ሰጠው ነው ይላሉ (2፡15-17)። እርስዋ ትዕዛዙን ከአዳም እንጂ፥ ከእግዚአብሔር አልሰማችም። ምንም እንኳ በቀጥታ ከእግዚአብሔር ላትሰማ ብትችልም፥ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ የመታዘዝ ኃላፊነት ግን ነበረባት።

28ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ለመታዘዝ የሚረዳቸው እየመሰላቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ሕግጋት ላይ የሚጨምሩት በምን መንገድ ነው?

ለ) ይህ ለክርስቲያኖች አደገኛ ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው?

3. ፈታኙ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ በመካድ ዓላማዎቹን አጠያያቂ አድርጎ ያቀርባቸዋል (ቁ. 4-5)

ሔዋን በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ላይ እንዴት እንደጨመረች በማየቱ፥ ሰይጣን የበለጠ ድፍረት አገኘ። በመጀመሪያ፥ የእግዚአብሔርን ቃል ካደ። መልካምና ክፉ ከምታሳውቀው ዛፍ መብላት ሞትን እንደማያመጣ ተናገረ። ሰይጣን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ባለመታዘዝ ሊመጣ የሚችል ጉዳት የለም ማለቱ ነበር። ለኃጢአት ቅጣት ከሌለው፥ ኃጢአትን ለመሥራት የሚያስፈራ ነገር አይኖርም ማለት ነው። ነገር ግን ኃጢአት ቅጣትን እንደሚያስከትል መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያሳያል። የኃጢአት ፍሬ ሁል ጊዜም ሞት ነው። ሰው አንድ ጊዜ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት መጠራጠር ከጀመረ፥ ቀጣዩ ደረጃ እግዚአብሔርን በቀጥታ መካድ ነው።

ሁለተኛ፥ አለመታዘዝን ቀላል ለማድረግ፥ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ መታዘዝ በሚያስፈልግባቸው ምክንያቶች ላይ ሰይጣን ጥርጣሬ ፈጠረ። እግዚአብሔር ትዕዛዛቱን የሰጠው ቀናተኛ ስለሆነ እንጂ፥ ለአዳምና ሔዋን ባለው ፍቅርና አሳቢነት እንዳልሆነ ተናገረ። ሞትን በማስከተል ፈንታ፥ ፍሬዋን መብላት መልካሙንና ክፉን ለማወቅ እንደሚያስችል

በማከል ተናገረ። በዚያን ጊዜ አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር ጋር እኩል ይሆናሉ ማለት ነው። በእራሳቸው ሕይወት ላይ ሙሉ ቁጥጥር ይኖራቸዋል። በእግዚአብሔር ከመገዛት ነጻ ይሆናሉ። እግዚአብሔርን ከመታዘዝ ይልቅ፥ እነርሱ እራሳቸው እንደአግልከት በሕይወታቸውና በዕጣ-ፈንታቸው ላይ ይገዛሉ።

ሰው ለጥቅሙ የሚውለው ምን እንደሆነና እንዳልሆነ የመወሰን ኃይል አልንበረውም። ይህ የአምላኩ የፈጣሪነት መብት ነው። ሰው የራሱን ፍላጎት ማዕከላዊ በሚያደርግበትና በፍላጎቱ ላይ ብቻ በመንተራስ በሚመርጥበት ጊዜ፥ እንደእግዚአብሔር ለመሆን እየሞከረ ነው ማለት ነው።

ምንም እንኳ አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር ቢፈጠሩና የሚኖሩበትንም ውብ ሥፍራ ቢሰጣቸውም፥ አሁን እግዚአብሔርን መጠራጠር ጀመሩ። እንደእውነቱ ከሆነ እግዚአብሔር የሰጣቸው ሁሉ መልካም ስለነበር፥ የሚያውቁትም ይህንኑ ነበር። ዳሩ ግን እግዚአብሔርን ባለመታዘዝ የሚያጠፋቸውን ክፉት አወቁ።

29ኛ ጥያቄ፡- የሔዋን ፈተና፥ እኛም ኃጢአት ከመሥራታችን በፊት በአእምሮአችን ውስጥ ከሚመላለሰው አሳብ ጋር እንዴት ይመሳሰላል?

4. የአዳምና ሔዋን በኃጢአት መውደቅ (ቁ. 6-7)

ሔዋንን በመፈተኑ ሂደት ውስጥ ተልዕኮውን ካሳካ በኋላ፥ ሰይጣን ዝምታን መረጠ። ሰይጣን ወንድን ወይም ሴትን ኃጢአት ለማሠራት አይችልም። ዳሩ ግን እነርሱን በመፈተን፥ አሳባቸውን ለማወዛገብ ሊጥር ይችላል። በመጨረሻም ኃጢአትን ለመፈጸም መምረጥ ያለበት ሰው ነው። ሰዎች ኃጢአትንና ክፋትን በእግዚአብሔር፥ በሌሎች ሰዎች፥ ወይም በሁኔታዎች ለማሳበብ ይፈልጋሉ። በመጨረሻው ግን፥ ኃጢአትን በምንሠራበት ወቅት የእያንዳንዳችን ምርጫ ነው።

30ኛ ጥያቄ፡- ሰዎች ኃጢአት በሚሠሩበት ጊዜ ተጠያቂ ለመሆን የማይፈልጉትና ዳሩ ግን ሌሎችን ሰዎች ወይም ነገሮች የሚኮንኑት ለምን ይመስልሃል?

ምንም እንኳ እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ከመታዘዝ በቀር ያለ ሌላ ምርጫ ሊፈጥራቸው ቢችልም፥ ሰው የመሆን አንዱ አካል ግን ለመታዘዝ ወይም ላለመታዘዝ የመምረጥ ችሎታ መሆኑ መዘንጋት የለበትም። ሔዋን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝና የትዕዛዙንም ምክንያቶች መጠራጠር በመጀመሯ፥ ውድቀቷ ቀረበ። ሔዋን እግዚአብሔር እንደሚቀጣት ማመኗን አቁማ ነበር። አየች፤ ፍሬው ለዓይን ያማረ ነበር። ተመኘች፤ እውቀትም ለማግኘት ፈለገች። መልካም በመሰለው ነገር ላይ በማተኮር፥ ክፉ የሆነውን መመልከት ዘነጋች። ወስዳም በመብላት ኃጢአት ሠራች። ሰይጣን በሔዋን ሰሜቶች፥ ዕውቀትና ፈቃድ በመጠቀም በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት እንድትሠራ አደረገ።

የኃጢአቷ አቢይ ምክንያት ምን ነበር? በገዛ ሕይወቷ ላይ ለመግዛት የነበረው ፍላጎቷ ነው። ለእግዚአብሔርና ለትዕዛዙ ብትገዛና እግዚአብሔር ከሰጣት በላይ ባትመኝ ኖሮ፥ ባልወደቀች ነበር። ዳሩ ግን በእርስዋነቷ ስላልረካችና የገዛ ሕወቷን ለምምራት ስለፈለገች፥ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ሠራች።

31ኛ ጥያቄ፡- ሔዋን በ1ኛ ቆሮ. 10፡14እና 2ኛ ጢሞ. 2፡22 ያለውን ትዕዛዝ ብትታዘዝ ኖሮ፥ ከኃጢአት እንዴት ታመልጥ ነበር?

የሚያሳዝነው ኃጢአት የአንድን ሰው ሕይወት በማጥፋት ብቻ ሳይገታ፥ ሁል ጊዜ የሌሎችንም ጥፋት ማስከተሉ ነው። በመጀመሪያ የእውቀትን ዛፍ ፍሬ የበላችው ሔዋን ነበረች። በዚያን ጊዜ አዳም የት እንደነበረ አናውቅም። አንዳንዶች ምላሽ ባይሰጥም አዳም አብሮአት እንደነበረ ይናገራሉ (በንግግራቸው ውስጥ ሰይጣን ‹እናንተ› የሚል የብዙ ስም ሲጠቀም፥ ሔዋንም ‹እኛ› እያለች ተናግራለች)። ወይም አዳም በሌላ ሥፍራ ሊሆን ይችላል። ዳሩ ግን ሔዋን ፍሬውን ከበላችና ያደረገችውንም ነገር ከተገነዘበች በኋላ፥ ለአዳምም እንዲበላ ሰጠችው። ከሔዋን በተቃራኒ፥ አዳም ፍሬውን ለመብላት በሰይጣን አልተታለለም ነበር። ዳሩ ግን እግዚአብሔርን ከመታዘዝ ይልቅ፥ ከባለቤቱ ጋር ለመወገን ፈልጎ፥ እያወቀ የኃጢአትን መንገድ በመምረጥ ፍሬውን በላ (1ኛ ጢሞ. ፡14)።

መጽሐፍ ቅዱስ «የሁለቱም ዓይኖች ተከፈቱ» ይላል። ይህ ማለት ዓይነ-ስውሮችና ለማየት የማይችሉ ነበሩ ማለት አይደለም። ይልቁንም ስለ ግብረ-ገባዊ ዓይናቸው የሚናገር ነው። አስቀድሞ አዳምና ሔዋን ንጹሐን ሳሉ፥ የሚያውቁትም የሚያደርጉትም መልካሙን ብቻ ነበር። ምንም ክፋት አያውቁም ነበር። አሁን ግን ክፉን መርጠው ነበር። በፊት ከሚያውቁት በላይ ቢያውቁም፥ ያወቁት ክፋትን እንጂ መልካምን አልነበረም። ከዚህ በመቀጠል እግዚአብሔር በተቀሩት ፍጥረታትና በሰው ውስጥ የፈጠራቸው መልካም ነገሮች ሁሉ፥ በዚህ አንድ ኃጢአት ሳቢያ እንዴት በክፋት እንደተበላሹ እንመለከታለን።

የኃጢአታቸው ውጤቶች ወዲያውኑ ተስተውለዋል። አራት ነገሮች እንደተፈጸሙ ተገልጿል።

1. የእውቀት ዓይኖቻቸው ተከፈቱ። ያደረጉትን ነገር ተገነዘቡ። የንጽሕናቸውን መልካምነት አጥተው በምትኩ ክፋታቸውን አወቁ።

2. እነርሱ ራሳቸው ዕራቁታቸውን መሆናቸውን ተረዱ። ትናንትና እንደተመለከተነው፥ ዕራቁትነታቸውን አለማወቃቸው (2፡25) በሴትና በወንድ መካከል በነበረው ግንኙነታቸው፥ ፍጹም ግልጾች በመሆናቸው ንጹሐን የመሆናቸው ምልክት ነበር። በፍጹም ስለ እራሳቸው የሚገዳቸው አልነበሩም። አሁን ግን እያንዳንዳቸው ወደ እራሳቸው በተመለከቱ ጊዜ፥ ለመጀመሪያ ጊዜ ራስ-ወዳዶች ሆኑ። ልዩነታቸውን አወቁ። አንዳቸው ለሌላቸውና ለራሳቸው ኃፍረት ተሰማቸው። ግሩም የነበረው የጋብቻ ግንኙነት መሻከር ጀመረ። የግንኙነታቸውም ግልጽነት አከተመ። ወዲያው ወንዱና ሴቷ እርስ በእርሳቸው መወቃቀስ ጀመሩ።

3. ሮጠው ከእግዚአብሔር ተደበቁ። በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የነበረው ግንኙነት ተቋረጠ።

32ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ይህ የተቋረጠው ግንኙነት በዛሬው ጊዜ የሚታየው እንዴት ነው?

ለ) ኃጢአት የምንሠራው ራስ-ወዳድ በመሆናችን እንደሆነ ለመናገር የምንችለው በምን መንገድ ነው?

4. እራሳቸውን በቅጠል ሸፈኑ። በዚህ ጊዜ ንጹሐን አልነበሩምና እግዚአብሔር እንዴት እንደ ፈጠራቸው በማየት አፍረዋል። ኃፍረት- ሥጋቸውን በቅጠሎች ሸፈኑ። ስሜታቸውንም መደበቅና መሸፋፈን ጀመሩ። ስለሆነም ዛሬ ሰዎች ጉዳታቸውን፥ ፍርሃታቸውን፥ ወይም ፍላጎታቸውን እርስ በእርሳቸው በግልጽ ለመነጋገር ይፈራሉ። በሕይወት ዘመናችን ሁሉ እውነተኛውን እኛነታችንን ሸፍነን እንኖራለን። ቅጠሎችም ሌላ ነገር ያመለክታሉ። ሰው ኃጢአቱን በእራሱ ዘዴዎች ለመሸፈን የሚያደርገውን የማያቋርጥ ጥረት ይጠቁማሉ። ደህንነታችንን በራሳችን ልናመጣው እንሞክራለን። ዳሩ ግን እንደቅጠሎቱ ሁሉ፥ ዘዴዎቻችንም የማይጠቅሙ፥ ጊዜያዊና፥ የተሳካ ውጤት የማያመጡ ናቸው።

33ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ይህን በሕይወትህ ሲፈጸም ያየኸው እንዴት ነው?

ለ) ክርስቲያኖች እንደመሆናችን እርስ በእርሳችን ታማኞች በመሆን፥ ጉዳቶቻችንን፥ መሻቶቻችንን፥ ወዘተ. መገላለጽ እንደሚገባን ይህ ምን ሊያስተምረን ይችላል?

በነገው ክፍለ- ትምህርታችን የዚያን የመጀመሪያ ኃጢአት ሌሎች ውጤቶች እነመለከታለን። ዘፍ. 3፡1-7 ኃጢአት እንዴት ክርስቲያንን በተደጋጋሚ እንደሚያጠቃ የሚያሳይ ምሳሌ ነው። የሚከተሉትን ነገሮች አስተውል፡-

1. የክርስቲያን ጠላቱ ሰይጣን ነው። በመሆኑም ክርስቲያኑን በኃጢአት ለመጣል የሚችለውን ሁሉ ከማድረግ አይቆጠብም። እያንዳንዳችን በቅድስና እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር ያወጣውን እቅድ እንዳንከተል ሲዋጋ ይኖራል። ዳሩ ግን ሰይጣን ኃጢአት ሊያሠራን አይችልም። አእምሮአችንን ለመለወጥ ቢተጋም፥ ኃጢአትን የምንሠራው ግን በራሳችን ነጻ ምርጫ ነው።

2. ሰይጣንን ለማሸነፍ ብቸኛውና ውጤታማው መንገድ፥ ሊያጠቃን እንደጀመረ ወዲያውኑ እርሱንና መሣሪያዎቹን ትቶ መሸሽ ነው። ከሰይጣን ጋር እየተጫወትንና አእምሮአችንን እንዲበርዝ እየፈቀድንለት፥ በቅድስና ልንኖር አንችልም።

3. ሰይጣን ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖችን ለመጣል ብቸኛ የሚሆኑበትን አጋጥሚ ይጠቀማል። አዳምና ሔዋን አብረው ቢሆኑ ኖሮ ላይወድቁ ይችሉ እንደ ነበረ ሁሉ፥ እኛም ከክርስቲያን ወገኖች ጋር ከሆንን፥ እንዲህ በቀላሉ በኃጢአት አንወድቅም። ብዙውን ጊዜ ከሌሎች ክርስቲያኖች አጠገብ ሳለን ኃጢአት አንሠራም። ከክርስቲያኖች ስንርቅ፥ ብቻችንን፡ ወይም ከማያምኑ ሰዎች ጋር ስንሆን ነው ሰይጣን በቀላሉ የሚያሸንፈን።

4. ኃጢአት ምን እንደሆነ ትክክለኛ መረዳት እንዳይኖረን፥ ሰይጣን የእግዚአብሔርን ቃል ያዛባል። ብዙ ሰዎች፥ የእግዚአብሔርን ሕግጋት ለመታዘዝ ባለመፈለግ፥ ለአራሳቸው ፍላጎት እንደሚመች አድርገው ይለውጡታል። ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ቃል በግልጽና በትክክል ማወቅ አለበት። ለእዚህ ነው መዝሙረኛው፥ «አንተን እንዳልበድል፥ ቃልህን በልቤ ሰወርሁ» [መዝ (119)፡ 11] ያለው።

5. እንዲሁም ሰይጣን የእግዚአብሔርን አሳቦች እንድንጠራጠር ይፈልጋል። እግዚአብሔርን የሕይወታችን ፈጣሪና ጌታ ከማድረግ ይልቅ፥ የምንፈልገውን ለማድረግ እንዲመቸን፥ የአራሳችን ሕይወት ገዥ ለመሆን እንድንሻ ይገፋፋናል። ለእግዚአብሔር መገዛት ይከብደናል። ነገሮች እንደምንፈልጋቸው ሳይሆኑ ሲቀሩ፥ ወዲያውኑ እግዚአብሔርን መጠራጠር እንጀምራለን። ከተሻለ ሕይወት፥ ከደስታ፥ ዓለምን ከመምሰል የሚያግደን ይመስለናል። ዓለምን እየተመለከትን፥ ከእኛ ይልቅ ጠቢብ ስለምትመስለን፥ እናደንቃታለን። ዳሩ ግን የእግዚአብሔር ቃል፥ እውነተኛ ጥበብ የሚመጣው እግዚአብሔርን በመፍራትና በመታዘዝ እንደሆነ ይነግረናል (ምሳሌ 1፡7)። የሰው ዕውቀት ወደ ጥፋትና ክፋት ይመራል። እንደ እውነቱ ከሆነ፥ እግዚአብሔር ሕግጋትን ለሰው ልጆች ሲሰጥ፥ ዓላማው እነርሱን ለመጉዳት ሳይሆን፥ በጎነታቸውን ለመጠበቅና ለመልካም ነው።

6. ኃጢአት ሁል ጊዜም መልካም ይመስላል። ልክ አይጢን ወደ ወጥመድ ውስጥ እንድትገባ የሚማርካት በወጥመዱ ውስጥ

የተቀመጠ ጣፋጭ ምግብ እንደሆነ ሁሉ፥ እንዲሁም ሰይጣን ሁል ጊዜ ኃጢአት መልካም እንዲመስል በማድረግ ክፋቱን ይሸሽጋል።

7. ኃጢአት ተላላፊ በሽታ በመሆኑ ሁል ጊዜም ሌሎችን ይበክላል። ኃጢአት ሕይወታችንን ማበላሸት ብቻ ሳይሆን፥ የሚስቶቻችንን፥ የልጆቻችንን፥ የቤተ ክርስቲያናችንን፥ ወዘተ. ሕይወትም ያጠፋል።

34ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ሰይጣን አንተን በኃጢአት ለመጣል ተመሳሳይ ዘዴዎችን የተጠቀመው እንዴት ነው?

ለ) በኃጢአት ላለመውደቅ የምታደርጋቸውን ጥረቶች ዘርዝር።

ሐ) አዳዲስ ክርስቲያኖች ሰይጣንን እንዴት እንደሚያሸንፉት ምን ምክር ትሰጣቸዋለህ?

ሦስተኛ ቀን :-ዘፍጥረት 3፡8-24

ዓለም በክፋት የተሞላችው ለምንድነው? ጦርነቶችና የዘር መከፋፈል የሚስተዋለው ለምንድነው? ረሃብና የምድር መናወጥስ ለምን ይከሰታል? ብዙ ጉስቁልና፥ ሕመምና ሞት የሚታየውስ ለምንድነው? እነዚህ ሁላችንም የምንጠይቃቸው የተለመዱ ጥያቄዎች ናቸው። ምንም እንኳ በሕይወታችን ዙሪያ ለሚፈጸሙት ዝርዝር ነገሮች ሁሉ መልስ ባናገኝላቸውም፥ በመጠኑም ቢሆን ዘፍጥረት 3፡8-24 መልካሙ የእግዚአብሔር ፍጥረት ለምን በሐዘንና በክፋት እንደተሞላ ይነግረናል። የመጀመሪያዎቹ ወንድና ሴት በኃጢአት በመውደቃቸው፥ መልካሙ የእግዚአብሔር ፍጥረት እጅግ በከፋ ሁኔታ ተለወጠ። ኃጢአት ፍጥረትን፥ ምድርን፥ አዳምና ሔዋንን፥ ሁሉንም ነገር ተጸናወተ። እግዚአብሔር አስቀድሞ ነገሮችን ሁሉ ሲባርክ፥ አሁን ግን መርገም፥ ወይም ፍርድ በፈጠራቸው ሁሉ ላይ ወረደ። ዳሩ ግን በፍርድ ውስጥም እንኳ የእግዚአብሔርን ምህረት እናያለን።

35ኛ ጥያቄ፡- ዘፍጥረት 3፡8-24 አንብብ።

ሀ) በቁጥር 8፥ እግዚአብሔር ከሰው ጋር ስለነበረው ግንኙነት ምን እንማራለን?

ለ) በእግዚአብሔር የተረገሙትን በሙሉ ዘርዝርና ዛሬ እንዴት የእነዚህን መርገሞች ውጤት እንደምንመለከት ግለጽ።

ሐ) በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የእግዚአብሔር ምህረት የተገለጸው እንዴት ነው?

መ) በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የኃጢአት አስከፊነት የታየው እንዴት ነው?

1. እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን ንሰሐ እንዲገቡ ይፈልጋል (ቁ. 8-13)።

ትናንትና እንደተመለከትነው፥ አዳምና ሔዋን ኃጢአት በሠሩ ጊዜ ኃጢአታቸው ቅጽበታዊ ፍርድ አስከትሎባቸው ነበረ። ህብረታቸውንና አንድነታቸውን፥ ግልጽነታቸውንና ንጽሕናቸውን አጡ።

ዳሩ ግን ከሁሉም የከፋው የኃጢአታቸው ውጤት፥ ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸው ህብረት ወዲያውኑ መቋረጡ ነው። ከቁጥር 8 ላይ እንደተመለከተው፥ አዳም፥ ሔዋንና እግዚአብሔር በየዕለቱ ህብረት ለማድረግ የመገናኘት ልምድ ያላቸው ይመስላል። ይህንንም የሚያደርጉት «ቀኑ በመሸ ጊዜ» ነበር። ዳሩ ግን ኃጢአት በሠሩበት ቀን፥ የእግዚአብሔርን መምጣት በሰሙ ጊዜ፥ አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር ተሸሸጉ። የወሰዱትን እርምጃ አስተውል። ወደ እግዚአብሔር ዘንድ ሂደው ይቅርታ በመጠየቅ ፈንታ፥ ከእግዚአብሔር ተሸሸጉ!! የሚያሳዝነው፥ ኃጢአት በምንሠራበት ጊዜ፥ ባመዛኙ የመጀመሪያው እርምጃችን ኃጢአትን ተናዝዞ ዳግም ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ለማድረግ ከመሻት ይልቅ፥ ኃጢአትን ለመሸሸግ መሞከር ነው።

36ኛ ጥያቄ፡- ኃጢአትን በምትሠራበት ወቅት ይህ በሕይወትህ ምን ያህል እውነት ነው?

እጅግ ከሚያስደንቁ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች አንዱ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ህብረት ለማድረግ ኃጢአተኛውን ሰው መፈለጉ ነው። ሰው ከእግዚአብሔር ቢሸሸግም፥ የተበላሸውን ህብረት ለማደስ መሥራት ያለበት እግዚአብሔር ነው። የእግዚአብሔርን ድምፅ

በመስማት አዳምና ሔዋን ተሸሸጉ። ይህ በእርግጥ ዋጋ የሌለው ነገር ነው። እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ስለሚያይና ስለሚያውቅ፥ ሰው ከእግዚአብሔር ሊሸሸግ አይችልም [መዝ. (139)]። እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ተከታታይ ጥያቄዎችን መጠየቅ ጀመረ። ይህን ያደረገው ያላወቀውን ነገር ለማወቅ ሳይሆን፥ አዳምና ሔዋን ኃጢአታቸውን እንዲናዘዙ በር ለመክፈት ነበር። ኃጢአትን መናዘዝ ለህብረቱ መስተካከል የመጀመሪያው አስፈላጊ ነገር ነው። ኃጢአታችንን ለእግዚአብሔርና ለበደልናቸው ሰዎች እስካልተናዘዝን ድረስ፥ የተበላሸው ህብረት ሊስተካከል አይችልም። እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን የት እንደተሸሸጉና፥ ኃጢአትን እንደሠሩ ያውቃል። ዳሩ ግን ስህተታቸውን እንዲቀበሉ ፈለገ። ይሁንና ከአዳምና ሔዋን ምላሽ፥ እኛ ኃጢአት በምንሠራበት ወቅት የምንሰጠውን የተለመደ ምላሽ እንመለከታለን።

37ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ብዙውን ጊዜ ኃጢአት ስንሠራ ምን እናደርጋለን?
የአዳምንና የሔዋንን ምላሽ ተመልከት።

ለ) ለኃጢአታቸው ማንን ተጠያቂ አደረጉ?

በቅድሚያ እግዚአብሔር ያነጋገረው መጀመሪያ የፈጠረውን አዳምን ነው። አዳም ሳይታለል እያወቀ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ሠርቷል። ዳሩ ግን መልካምና ክፉ ከምታሳውቀው ዛፍ ፍሬ በልቶ እንደሆነ እግዚአብሔር ሲጠይቀው፥ ‹በላሁ› በማለት ኃጢአቱን ተናዝዞአል። ዳሩ ግን ለእራሱ ኃጢአት ጥፋቱን በማመን ፈንታ፥ በሌሎች ላይ ማላከክ ጀመረ። በመጀመሪያ፥ ጥፋቱን በሔዋን አላከከ። ፍሬውን የሰጠችኝ ሔዋን ነች አለ። ዳሩ ግን ሔዋን ፍሬውን ብትሰጠውም፥ እንዲበላ አላስገደደችውም በእራሱ ነጻ ምርጫ በልቷል።

ሁለተኛ፥ አዳም እግዚአብሔርንም ጥፋተኛ አድርጓል። እግዚአብሔር ሴትን ስለ ሰጠው፥ ኃጢአቱ የመጣው በእግዚአብሔር ጥፋት ነው ብሏል። እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሔዋንን ሲፈጥር፥ ለአዳም መልካም በማሰብ ስለ ነበር፥ አዳምም በመፈጠሯ ደስ ተሰኝቶ ነበር። አሁን ግን ጥፋቱን በመቀበል ፈንታ፥ ሔዋንን ለጥፋቱ ተጠያቂ አደረጋት። ለመጀመሪያ ጊዜ፥ በቤተሰብ ውስጥ መከፋፈልንና በባልና

ሚስት መካከል የህብረትን መታጣት እንመለከታለን። እውነተኛው ‹አንድነት› በምንም ዓይነት ሙሉ ለሙሉ ዳግም ሊታደስ በማይችልበት ሁኔታ ተናጋ።

38ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ዛሬ ይህ የባሎችና የሚስቶች ህብረት ማጣት የሚታየው እንዴት ነው?

ለ) ክርስቲያኖች ያንን አንድነት በከፊል ለማግኘት ምን ማድረግ ይችላሉ?

አዳም እያቅማማም ቢሆን ከፍሬዋ እንደበላ ስለተናዘዘ፥ ኃጢአቷን ትናዘዝ እንደሆነ ለማየት እግዚአብሔር ወደ ሔዋን ዞረ። እንደአዳም ሁሉ እርሷም ‹በልቻለሁ› አለች። ዳሩ ግን በራሷ ነጻ ምርጫ እንደ በላች በማመን ፈንታ፥ እርስዋም ጥፋቱን በሌላው ላይ አኖረች - በእባብ ላይ።

ይኸው ተመሳሳይ ምላሽ ብዙውን ጊዜ ኃጢአት በምንሠራበት ጊዜ ይታያል። አንድን ነገር እንዳበላሸን ወይም ኃጢአት እንደሠራን በመቀበል ፈንታ፥ «ተበላሽብኝ» እንላለን። ወይም የሆነ ሁኔታ ወይም ሌላ ሰው እንወቅሳለን። እውነተኛና ተአማኒነት ያለው ንስሐ የሚመጣው ኃጢአት እንደሠራንና ጥፋተኞች እንደሆንን በግልጽ ስንቀበል ነው።

39ኛ ጥያቄ፡- መዝ. (51) አንብብ።

ሀ) የዳዊትን ኑዛዜ ከአዳምና ሔዋን ጋር አወዳድር።

ለ) የዳዊት የሚሻለው ለምንድነው?

ሐ) ከዳዊት የንስሐ ጸሎት ምን ትምህርት መማር አለብን?

መ) ዳዊትን የበለጠ ለመምሰል፥ በሕይወታችንና በቤተ ክርስቲያናችን መለወጥ የሚያስፈልጋቸው የንስሐ ልምምዶች የትኞቹ ናቸው?

ሠ) በሕይወትህ ንስሐ ያልገባህባቸው ኃጢአቶች አሉን? ከሆነ፥ አሁኑኑ ለእግዚአብሔር እና ካስፈለገም ለበደልሃቸው ሰዎች ተናዘዝ።

2. እግዚአብሔር የኃጢአትን ቅጣት አስታወቀ (ቁ. 14-19)

ኃጢአታቸውን ሲናዘዙ፥ እግዚአብሔር ሁል ጊዜም ኃጢአት አሉታዊ ውጤቶች እንዳሉት ማሳየት ጀመረ። ብጥብጥ፥ ጥፋትና ሞትን ያመጣል። በመጀመሪያ ኃጢአት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ሊመስል ቢችልም፥ ፍጻሜው ግን ሁል ጊዜም ጥፋት ነው።

40ኛ ጥያቄ፤ ይህ በሕይወትህ የታየው እንዴት ነው?

የኃጢአትን ኑዛዜ ከተቀበለ በኋላ፥ በአራት ነገሮች ላይ ርግማንን አወረደ ወይም ፍርድን አዘዘ፡-

1. እግዚአብሔር በእባቡ ላይ ፈረደበት (ቁ. 14-15)። በእባቡ ርግማን ውስጥ ሁለት ነገሮች ተረግመዋል። በመጀመሪያ፥ አካላዊው እባብ ከሰይጣን ጋር በማበሩ ተረግሟል። የእንስሳት የበላይ በመሆን ፈንታ፥ በመሬት ላይ በሆዱ እየተሳበ ዝቅ ብሎ ይኖራል። የእባብ ሥጋዊ አካል የተለወጠውና አሁን በሆዱ እየተንቋቀቀ የሚሄደው ከእዚህ የተነሣ ነው። ሁል ጊዜም በመሬት ላይ መኖር ስላለበት፥ የምድር አፈር በላዩ ላይና ከምግቦቹም ጋር ይቀላቀል ነበር። የምድርንም አፈር መብላት ነበረበት። እንዲሁም በሰው ልጅና በእባቦች መካከል የተለየ ጠላትነት ይኖራል። ይህ ዛሬ ሰዎች በእባቦች ላይ ባላቸው ፍርሃት ይታያል። ሁለተኛ እግዚአብሔር ከእባቡ ጀርባ የነበረውን ሰይጣንንም ረግሞታል። ዘፍጥረት 3፡15 በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የመጀመሪያው ትንቢት ሲሆን፥ በኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት ፍጻሜ ያገኘ ክፍል ነው። ይህን ጥቅስ መረዳት የሚቻልባቸው ሁለት መንገዶች አሉ። በመጀመሪያ፥ በሴቲቱ ዘር (በዘመናት ሁሉ ያሉ የእግዚአብሔር ልጆች) እና በእባቡ ዘር (ክፉው) መካካል ያለውን የማያቋርጥ ጠላትነት ሊያመለክት ይችላል። ምንም እንኳ መጀመሪያ ክፉው የእባብ ዘር የእግዚአብሔርን ልጆች ቢጎዳም፥ ከፍተኛውና የመጨረሻው ድል የእግዚአብሔር ልጆች ነው። የክፉውን እራስ ይቀጠቅጣሉ።

41ኛ ጥያቄ፡- የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከት፡- (ዮሐ. 16፡30፤ 1ኛ ዮሐ. 4፡4፤ ራእይ 12፡11፤ 17፡14)። መጽሐፍ ቅዱስ ለጻድቅ ሰው የሚሰጣቸው የተስፋ ቃላት ምንድናቸው?

ዳሩ ግን ዘፍ. 3፤15 በይበልጥ የሚያመለክተው በሰይጣንና የሴቲቱ ዘር በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ (የኢየሱስን ሰው መሆን ሲያመለክት) መካከል የሚደረገውን ታላቅ ጦርነት ነው። ምንም እንኳ ሰይጣን የኢየሱስን ሰኮና በስቅለት ቢቀጠቅጥም፥ ኢየሱስ የሰይጣንን እራስ ይቀጠቅጣል። ይህም መጀመሪያ በመስቀል ላይ የተከናወነ ሲሆን፥ በዘመናት መጨረሻ ሙሉ ለሙሉ ይፈጸማል (ራእይ 20፡10)።

42ኛ ጥያቄ፡- ይህ ትንቢት ለእኛ መጽናኛ የሚሆነን እንዴት ነት?

2. እግዚአብሔር በሴቲቱ ሔዋን ላይም ፍርድን አዝዞአል (ቁ. 16)። ሁለት ፍርዶችን አዘዘባት። ምንም እንኳ ልጅ የመውለድ አስደሳች ልምምድ ቢኖራትም፥ ልጅ የመውለዱ ሂደት ከፍተኛ የሕመም ሥቃይ ያስከትልባታል። ዛሬ ልጅ በሚወልዱበት ጊዜ ሴቶች ሁሉ ይህን ፍርድ ይቀበላሉ። ሁለተኛ በባልና ሚስት መካከል የነበረው የእኩልነት ግንኙነት ይቀራል። ከውድቀት በፊት፥ ሚስት ለባል የምትገዛበት ምክንያት አልነበረም፤ አሁን ግን እንዲገዛትና እንዲያዝዛት የበላይነት ለባል ተሰጠ። ኃጢአት በመሥራቱ ሂደት ሔዋን ቀዳሚውን ሚና ስለተጫወተች፥ እርስዋና ከእርስዋ በኋላ የሚመጡ ሴቶች በወንዶች በሚገዙበት ግንኙነት ለመኖር ተገደዱ።

43ኛ ጥያቄ፡- ዛሬ ይህ በዓለም ውስጥ የሚታየው እንዴት ነው?

ይህንን እርግማን ከዛሬው ሁኔታ ጋር እንዴት ማዛመድ እንደሚኖርብን የሚመሩን ሦስት ጠቃሚ እውነቶች በአዲስ ኪዳን ውስጥ ይገኛሉ፡- በመጀመሪያ፥ ወንድና ሴት እኩል እንደሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያስተምራል። ወንድ ከሴት በላይ አይደለም (ገላ. 3፡28 ተመልከት)።

ሁለተኛ፥ አሁንም ሚስት ለባልዋ የምትገዛበት ሁኔታ አለ። ይህም ባልና ሚስት ሁለቱም ኃጢአተኞች ስለሆኑና በዚህም ምክንያት በቤት ውስት አንድነትን ለመፍጠር የሥልጣን ተዋረድ ስላስፈለገ ነው (ኤፌ. 5፡22-31 ተመልከት)። ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ዓላማ ርግማኑን ማስወገድ በመሆኑ፥ ባልና ሚስት በክርስቶስ ባላቸው እምነት እየበሰሉ ሲሄዱ፥ ባል በሚስቱ ላይ የሚኖረው የበላይነት እየቀነሰ ይሄዳል። ሦስተኛ፥ በሴቷ ላይ የወንዱ የበላይነት የጭቆና ዓይነት አገዛዝ

አይደለም። የባልና ሚስት ግንኙነት ክርስቶስ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ካለው ግንኙነት ጋር ተወዳድሯል። ክርስቶስ በቤተ ክርስቲያን ላይ ሥልጣን ቢኖረውም፥ በነገር ሁሉ ለእርስዋ ባለው ፍቅር ተገዝቷል። የቤተ ክርስቲያንን ዕድገት ከእራሱ ፍላጎት በላይ ይሻል። በመሆኑም ለቤተ ክርስቲያን ሞቶላታል። እንደዚሁም ምንም እንኳ ውድ ዋጋ ሊያስከፍለው ቢችልም፥ ባል ለሚስቱ ያለው ፍቅር የእርስዋን ፍላጎት ከእራሱ በማስቀደሙ ሊረጋገጥ ይገባል።

44ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ይህ በባልና ሚስት መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ብዙዎች ከሚያስተምሩት ወይም ከሚለማመዱት እንዴት ይለያል?

ለ) እነዚህን እውነቶች በጋብቻህ ውስጥ እንዴት ለመተግበር እንደምትፈልግ ግለጽ።

3. ፍጥረት ተረግሟል (ቁ. 17-18)። እግዚአብሔር ሰውን በፈጠረ ጊዜ፥ የፈጠረው ሁሉ መልካም ነበር። ከሰው ጋር በመተባበር እንዲሠራ እንጂ፥ ከጥረቶቹ ሁሉ ጋር እንዲዋጋ አልተፈጠረም ነበር። አሁን ግን በአዳምና ሔዋን ውድቀት ሳቢያ፥ ፍጥረት በሙሉ በለውጥ ማዕበል ተመትቷል። አረሞችና እሾሆች ከሰው ጥረት ጋር መዋጋት ጀመሩ። ሁል ጊዜም የሰውን ልጅ የሚያውኩ እንደ በሽታ፥ ረሃብ፥ የምድር መናወጥና ሌሎችም ነገሮች መከሰት ጀመሩ።

45ኛ ጥያቄ፡- ሮሜ 8፡19-23 አንብብ። ይህ ጥቅስ እርግማኑ ምን እንደሚሆን ምን ሲል ይናገራል? መቼ?

4. አዳም ተረገመ (ቁ. 19)። ዛሬም እኛን የሚተናነቁን በአዳም ላይ የታዘዙ ሁለት ፍርዶች ነበሩ። ከውድቀት በፊት እግዚአብሔር ሁሉንም ዓይነት ምግብ ይሰጣቸው ነበር፤ አሁን ግን ሕይወት በድካም ሠርተው የሚበሉባት ሆነች። የሰው ልጅ በልቶ ሕይወቱን የሚያቆይበትን በቂ ምግብ ለማግኘት አድካሚ ሥራ መሥራት ነበረበት። ለቤተሰቡ ምግብ የማቅረብ ኃላፊነት የተጣለበት ባል በትልቅ ችግር ይህን ማድረግ ነበረበት። ሁለተኛ፥ አዳምና ሔዋን ልጆቻቸውም ሁሉ ሞትን መቅመስ ነበረባቸው። እግዚአብሔር

እነርሱን ለመፍጠር እንደተጠቀመባት ሁሉ፥ ሲሞቱ አካላቸው ወደ ምድር መመለስ ነበረበት።

ፍሬዋን በመብላት ለሚከተለው አለመታዘዝ፥ እግዚአብሔር የሰጠው ፍርድ ሞት ነበር። ይህ ሞት በሁለት መንገዶች መጥቷል። አዳምና ሔዋን ወዲያውኑ መንፈሳዊ ሞት ሞተው ነበር። ሞት ማለት መለየት ማለት ነው። መንፈሳዊ ሞት የሰው ከእግዚአብሔር መለየት ነው። ከኃጢአታቸው በኋላ በአዳም፥ በሔዋንና በእግዚአብሔር መካከል የነበረው ህብረት ተቋርጦ ነበር። መታደስም ያስፈልገው ነበር። ዳሩ ግን በመጨረሻ ሥጋቸውና መንፈሳቸው በሥጋዊ ሞት መለያየት ነበረበት።

46ኛ ጥያቄ፡- ዛሬ እነዚህ ሁለት የሞት ዓይነቶች የሚታዩት እንዴት ነው?

ሁላችንም በአንድ ወይም በሌላ መንገድ በአዳምና ሔዋን ኃጢአት እንደተሳተፍን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል (ሮሜ 5፡12-19)። የመጀመሪያ ወላጆቻችን እንደ መሆናቸው፥ አዳምና ሔዋን የእኛ ተወካዮች ናቸው። እኛም በዚያ ሥፍራ ተገኝተን በኃጢአታቸው እንደተባበርን ያህል ነው። ከዚህ የተነሣ ሁላችንም ኃጢአተኞች ነን። የአዳምና ሔዋን ኃጢአት አንድ ሌላ ውጤትም አለው። ይኸውም ልጆቻቸው ሁሉ የኃጢአትን ተፈጥሮ መውረሳቸው ነው። ሕፃን ልጅ በሚወለድበት ጊዜ እንኳ፥ እግዚአብሔርን ከመታዘዝ ይልቅ ኃጢአትን ለመምረጥ ያለው መሻት ወዲያውኑ ይታወቃል። ክርስቲያኖች ብንሆንም እንኳ፥ ይህ የኃጢአት ተፈጥሮ ሁል ጊዜም አብሮን አለ። ወደ ኃጢአት እየሳበ ሊወስደን ይታገላል።

47ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በሕይወትህ የኃጢአት ተፈጥሮ የሚታየው እንዴት ነው?

ለ) እንዴት አሸነፍኸው? (ሮሜ 6፤ ገላ. 5፡16-26)።

ከዚህ ታሪክ ውስጥ ልብ ማለት የሚያስፈልገው ጠቃሚ እውነት አለ። እግዚአብሔር ለአዳምና ሔዋን ይቅርታ ቢያደርግላቸውም፥ ኃጢአታቸው ግን ሙሉ በሙሉ ሊቋቋሙዋቸው የማይችሉዋቸውን ዘላቂ ውጤቶች አስከትሎባቸው ነበር። ብዙ ሰዎች ኃጢአት ቢያደርጉ፥

የኃጢአታቸውን ውጤት በቀላሉ የሚቋቋሙ ይመስላቸዋል። ማድረግ የሚችሉት ነገር ቢኖር ኃጢአታቸውን መናዘዝ ነው። ዳሩ ግን ሁል ጊዜም እንዲህ አይሆንም። ኑዛዜ ከእዚአብሔር ጋር የነበረንን ግንኙነት ያድስልናል። የኃጢአት ውጤቶች ግን እንዳሉ ናቸው። ለማስወገድ በዓመታት የሚቆጠር የጊዜ ገደብ የሚፈጅ የግል ጥፋት በሕይወታችን ውስጥ ተደጋግሞ ይፈጸማል። ከሌሎች ጋር የነበሩ ወዳጅነቶች መቋረጥ ይታያል። በሌላም በኩል የወደመችዋ ምድር አለች። ምንም እንኳ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት በንስሐ ቢታደስም፥ ብዙውን ጊዜ የኃጢአት ውጤቶች ይቀጥላሉ እንጂ፥ ወደ ፍጻሜ አይደርሱም።

48ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ዛሬ የእርግማን ውጤት የሚታየው እንዴት ነው?

ለ) የኃጢአታችን ውጤቶች እኛን፥ ሌሎችን፥ ወይም ዓለምን ማበላሸታቸውን የሚቀጥሉት በምን መንገድ ነው?

4. ለሰው ልጅ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታዎች (ቁ. 20-24)

እግዚአብሔር ጻድቅ ስለሆነ፥ ሁል ጊዜም በኃጢአት ላይ ይፈርዳል። አንዳንዶች እግዚአብሔር የፍቅር አምላክ ስለሆነ ኃጢአት ብንሠራም አይፈርድብንም ይላሉ። ዳሩ ግን እንደተመለከትነው፥ እግዚአብሔር ሁል ጊዜም ኃጢአትን ይቀጣል። የኃጢአታችንን መዘዞች በሕይወታችን ውስጥ እንለማመዳለን። ዳሩ ግን እግዚአብሔር ከፍቅሩ የተነሣ ለኃጢአታችን ትልቅ ዋጋ ከፈለልን። ዘላለማዊ የመንፈስ ሞት እንድንሞት በማድረግ ፈንታ፥ ለኃጢአታችን ዋጋ እንዲከፍልና እንዲሞትልን እግዚአብሔር ኢየሱስን ላከው።

እንዲሁም እግዚአብሔር ጸጋን የተሞላ አምላክ በመሆኑ፥ በዚህ ክፍል ውስጥ ለኃጢአተኛ የሚሰጠውን የጸጋ ስጦታ እንመለከታለን። ቀደም ብለን ያየናቸው ሁለት ስጦታዎች ነበሩ፡-

1. ምንም እንኳ ሞት እርግማን ቢሆንና ትልቅ ሐዘን ቢያስከትልም መልካም በረከትም አለው። እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ለመኖር ሲሉ ለዘላለም መታገላቸውን እንዲቀጥሉ ማድረግ ይችል ነበር። ዳሩ ግን እንዲሞቱና ከትግላቸው እንዲያርፉ ፈቀደ። ክርስቲያን ለሆንን ለእኛ፥ ሞት ኢየሱስ ወዳለበት ሥፍራ ይወስደናል። ሞት

‹መውጊያውን› አጥቷል። አንድ ቀን ሞት ድል በመነሳት ይዋጣል (ራእይ 20፡14፤ 21፡4)

2. ሰው በመጨረሻው በጠላቱ ሰይጣን ላይ ድልን እንደሚቀዳጅ ተስፋ ተሰጥቶታል። አንድ ቀን ሰይጣን ግብዓተ-መሬቱ ይፈጸማል።

በዚህ ክፍል ውስጥ የእግዚአብሔርን ጸጋ ስለሚያሳዩ ሌሎች ምልክቶች እናጠናለን።

3. እግዚአብሔር የሰውን ዘር ከምድር ላይ አላጠፋም (ቁ. 20)። ከእዚህ ቀደም ሲል ሔዋን በተፈጠረች ጊዜ «ሴት» ወይም «ሰውን የምትመስል» ተብላ በአዳም እንደተሰየመች ተመልክተናል። አሁን ደግሞ አዳም ሔዋን ብሎ በድጋሚ ይሰይማታል። ሔዋን ማለት «ሕያው፥ ሕይወት-ሰጪ»፥ ወይም «የሕያዋን ሁሉ እናት» ማለት ነው። አዳም ይህን ሲል፥ በእርስዋ አማካኝነት ሕይወት በምድር ላይ ይቀጥላል ማለቱ ነበር። የሰው ልጅ የሕይወት ዑደት ከማብቃት ይልቅ ይቀጥል ጀመር።

4. እግዚአብሔር የኃጢአተኞቹን ኃፍረት ሸፈነ (ቁ. 21)። ከራቁትነታቸው የተነሣ፥ እግዚአብሔር አሁን የእንስሳ ቆዳ አለበሳቸው። ይህም እራሳቸውን በቅጠል ለመሸፈን ካደረጉት ጥረት በጣም የተሻለ ነበር። ይሁንና ይህ ቆዳ አንድ ሌላ ነገር ያመለክታል። ለአዳምና ለሔዋን የእንስሳ ቆዳ ለማልበስ ሲባል የመጀመሪያው ሞት መጣ። አዳምና ሔዋን ቅጽበታዊ ሞት ከሚሞቱ ይልቅ፥ እግዚአብሔር የመጀመሪያዎቹን እንስሳት ገደለ። እነዚህ እንስሳት የመጀመሪያዎቹ የኃጢአት መሥዋዕት ሆኑ። በኃጢአተኛው ምትክ አንድን እንስሳ መግደል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለኃጢአት ይቅርታ ዘለቄታ ያለው መመሪያ ሆነ። በብሉይ ኪዳን ውስጥ፥ እግዚአብሔር የእንስሳት ደም ለጊዜው ኃጢአትን እንዲሸፍን ፈቅዷል። ዳሩ ግን በአዲስ ኪዳን፥ ኃጢአትን ሙሉ ለሙሉ የሚያነጻው የኢየሱስ ደም ነው (ዕብ. 9፡11-14 ተመልከት)። በኃጢአት ምክንያት በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ለተፈጠረው መለያየት መፍትሔ ሊያመጣ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የነበረው ህብረት ሊታደስ የሚችለው የደኅንነት መንገዱን በመቀበል ብቻ ነው።

49ኛ ጥያቄ፡- በዛሬው ጊዜ ሰዎች የኃጢአት ይቅርታንና ደኅንነትን ለማግኘት በእራሳቸው መንገድ የሚሞክሩት እንዴት ነው?

5. እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ከዔድን ገነት አስወጣቸው (ቁ. 22-24)።

በዔድን ገነት ውስጥ ሁለት ዛፎች እንደነበሩ ታስታውሳለህ። አዳምና ሔዋን ከተከለከለው መልካምና ክፉ ከሚያስታውቅ ዛፍ ፍሬ በመብላታቸው ኃጢአትን ወደ ዓለም አምጥተዋል። ምንም እንኳ ቀደም ብሎ ከሕይወት ዛፍ እንዲበሉ የተፈቀደላቸው ቢሆንም፥ አሁን እግዚአብሔር ከእዚህ ዛፍ ፍሬ እንዳይበሉ ከለከላቸው። እግዚአብሔር ለዘላለም በኃጢአት ሕይወት እንዲኖሩ አልፈለገም ነበር። ስለዚህ እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ከገነት አስወጣቸው። አዳምና ሔዋን ወደ ሕይወት ዛፍ ተመልሰው ለመብላትና ለዘላለም ለመኖር እንዳይፈተኑ፥ እግዚአብሔር ኪሩቤልን በዔድን ገነት መግቢያ ላይ አስቀመጠ።

በመጽሐፍ ቅዱስ፥ ኪሩቤል፥ የእግዚአብሔርን ቅድስናና ክብር ለመጠበቅ ዘወትር ከእግዚአብሔር ሕልውና ጋር እጅግ ቀርበው የሚገኙ መላእክት ናቸው (ኢሳ. 6፤ ሕዝ. 1፥10)።

ከዚህ በኋላ መልካምና ክፉ ስለምታሳውቀው ዛፍ የተጻፈ ነገር ባናገኝም፥ ስለ ሕይወት ዛፍ ግን እናነባለን። ስለዚህ በመጨረሻው እግዚአብሔር ወደ መንግሥተ-ሰማይ የወሰደው ይመስላል። በራእይ 22፡2 «በውንዙም ወዲያና ወዲህ በየወሩ እያፈራ አሥራ ሁለት ፍሬ የሚሰጥ የሕይወት ዛፍ ነበር፤ የዛፉም ቅጠሎች ለሕዝብ መፈወሻ ነበሩ» የሚል እናነባለን። የዘላለም ሕይወት አሁንም እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የሚሰጠው ተስፋ ነው። የሚገኘው ግን እግዚአብሔር ያዘጋጀውን መንገድ በመቀበል ብቻ ነው። ይኸውም ኢየሱስ ክርስቶስ ለኃጢአታችን በከፈለው መሥዋዕት በማመን ነው (ዮሐ. 3፡16)።

50ኛ ጥያቄ፡- ለኃጢአትህ የተከፈለውን የኢየሱስ መሥዋዕት ለመቀበልና የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን በግልህ የወሰንህበትን ሁኔታ ግለጽ።

አዳምና ሔዋን በኃጢአት በመውደቃቸው፥ የአዲስ ዘመን ጅማሬ እንመለከታለን። ይህም የኃጢአት፥ የሞትና የጥፋት ዘመን ነው። ኃጢአት እንዴት በፍጥነት በዓለም ሁሉ እንደተሠራጨ ነገ እንመለከታለን። ዳሩ ግን መማር የሚያስፈልገን ዋናው ቁም-ነገር፥ ኃጢአት ምንም ያህል ትንሽ ቢመስልም፥ ሥቃይና ከፍተኛ ጥፋት እንደሚያስከትል ነው። የአንድ የዛፍ ፍሬን መብላት ዓለምን አጥፍቷል። ኃጢአት፥ በምንሠራበት ሰዓት የኃጢአታችን መዘዝ ምን እንደሚሆን አናውቅም። ሁላችንም ኃጢአት ብንሠራም፥ ኃጢአታችንን በግልጽ ለእግዚአብሔር በመናዘዝ ዳግም ይቅርታ እንደምናገኝና ከእርሱም ጋር ወዳለን ህብረት እንደምንመለስ ማስታወስ አለብን።

51ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ይህ ታሪክ ስለ ኃጢአት አስከፊነትና ከእግዚአብሔርም ዘንድ እንዴት ይቅርታ እንደምናገኝ ምን ያስተምረናል?

ለ) ሕይወትህን መርምርና ኃጢአት ካለብህ እግዚአብሔርንና ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ሰዎች ይቅርታ ጠይቅ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አዳም በምሳሌነት ተጠቅሷል። የመጀመሪያው ሰው በመሆኑ፥ የሰብዓዊ ፍጥረት ሁሉ አባት ነው። የኃጢአት ተፈጥሮና ሞት ወደ ሰዎች ሁሉ የተላለፈው በእርሱ ኃጢአት ነው። የትም እንኑር፥ ምንም ያህል የተማርን እንሁን፥ ኃጢአት በሕይወታችን ውስጥ ይገኛል። ዳሩ ግን ከአዳም የተለየ ባሕርይ ያለው ሌላ ሰው መጣ። የአዳም ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ የተለየ ሕይወት ይዞልን መጣ። በእርሱም አዲስ መስመር ተዘረጋ - የዘላለም ሕይወት መስመር። ይህ መስመር የአዳም የተፈጥሮ ልጆች በመሆን ብቻ ሳይወሰኑ፥ በእምነት የእግዚአብሔር ልጆች ለሚሆኑት ሁሉ ክፍት ነው (ሮሜ 5፡12-21 ተመልከተ)።

አራተኛ ቀን ፡- ዘፍጥረት 4

ኃጢአት በከፍተኛ ፍጥነት የሚተላለፍ በሽታ ነው። ይስፋፋል። ዘፍ. 4-6 እንዴት ኃጢአት በፍጥነት በዓለም ሁሉ እንደ ተስፋፋ የሚናገር ታሪክ ነው።

52ኛ ጥያቄ፡- ዘፍ. 4ን አንብብ። ሀ) ጸሐፊው የኃጢአትን መስፋፋት እንዴት ያሳያል?

ለ) በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ጅማሬ ያገኙትን ነገሮች ዘርዝር።

ዘፍጥረት 4 የአዳምና ሔዋን ታላቅ ልጅ በሆነው በቃየን ላይ ያተኩራል። ኃጢአት እንዲሁም ሥልጣኔ እንዴት በፍጥነት በዓለም ሁሉ ላይ እንደተስፋፋ ለማሳየት፥ እርሱንና የቤተሰብ ሐረጉን ይገልጻል።

1. የቃየን ሕይወት (ቁ. 1-16)

አዳምና ሔዋን ከዔድን ገነት ከወጡ ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ሁለት ልጆችን ወለዱ። ታላቁ ቃየን ተባለ። ልክ እንደ አባቱ ቃየን ገበሬ ነበር። ቀጣዩ አቤል ተብሎ ተሰየመ። እርሱም እረኛ ነበር። ታሪኩ አሁን ከአዳምና ሔዋን ወደ ልጆቻቸው ይተላለፋል።

እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን መሥዋዕት እንዲያቀርቡ ያስተማራቸው ይመስላል። በብሉይ ኪዳን ሁለት ዋና ዋና የመሥዋዕት ዓይነቶች ነበሩ። የመጀመሪያው ዓይነት መሥዋዕት የኃጢአት መሥዋዕት ሲሆን፥ የእንስሳት ደም ማፍሰስን ያካትት ነበር። ይህንን እግዚአብሔር እንስሳትን በመግደል ቆዳቸውን ለአዳምና ለሔዋን ባለበሰበት በትላንቱ ትምህርት ውስጥ ተመልክተናል። ዳሩ ግን ቃየንና አቤል ለእግዚአብሔር ያቀረቡት መሥዋዕት የምስጋና መሥዋዕት ይመስላል። ይህም ሁለተኛው ዓይነት መሥዋዕት ነው።

ጸሐፊው እዚህ ላይ የተሠዋውን ነገር በማነጻጸር አላቀረበም። እግዚአብሔር አቤልን ያመሰገነው እንስሳትን ስላቀረበ አይደለም። ቃየንም ተቀባይነት ያጣው ከምድሪቱ ፍሬ የእህል መሥዋዕት ስላቀረበ

አይደለም። ሁለቱም ለመሥዋዕትነት የቀረቡ ነገሮች በኋላ በሙሴ ሕግ ውስጥ ተቀባይነት አግኝተዋል። እግዚአብሔር በይበልጥ ያተኮረው መሥዋዕቱን ባቀረቡት ሰዎች የልብ ዝንባሌ ላይ ነው።

መሥዋዕቱን በሚያቀርቡበት ወቅት የሁለቱ አምላኪዎች ዝንባሌ በጣም የተለያየ ነበር። አቤል ካለው ነገር ሁሉ እጅግ የሚሻለውን ለእግዚአብሔር ስላቀረበ እግዚአብሔርን አስደሰተ። በመጀመሪያ፥ ከመንጋው በኩሩን ለእግዚአብሔር ሰጠ። የመንጋው በጎች ከተባዙለት በኋላ ሳይሆን ለእግዚአብሔር የመጀመሪያውን ሰጠ። ሁለተኛ፥ ከእንስሳው አካል እጅግ የሚበልጥ ተደርጎ የሚቆጠረውን ስብ ለእግዚአብሔር ሰጠ። እነዚህ ሁለቱም አቤል ምን ያህል እግዚአብሔርን እንደ ወደደና ለሰጠውም ነገር በሙሉ ልቡ እንዳመሰገነው ያሳያሉ።

53ኛ ጥያቄ፡- እኛስ ዛሬ ይህንን የልብ ዝንባሌ በአምልኮአችን እንዴት እናሳያለን?

ዳሩ ግን ቃየን፥ ትክክለኛ የልብ ዝንባሌ አልነበረውም። ቃየን ለእግዚአብሔር ከእህሉ ሁሉ የተሻለውን ወይም የበኩራቱን እንደ ሰጠ የሚያመለክት ነገር የለም። ከምርቱ ወደ እግዚአብሔር ያመጣው በዘልማድ ብቻ ነበር። የአቀራረቡ ዝንባሌ ትክክል እንዳልሆነ በመናገር እግዚአብሔር ሲያስጠነቅቀው፥ ተጸጽቶ ንስሐ በመግባት ፈንታ፥ ቃየን በቅንዓት ተሞላ። በእግዚአብሔርና በወንድሙም ላይ ተቆጣ።

54ኛ ጥያቄ፡- ቃየን የተቆጣውና ንስሐ ያልገባው ለምንድነው?

55ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ዛሬ ብዙ ክርስቲያኖች በተሳሳተ ዝንባሌ እግዚአብሔርን የሚያመለኩት እንዴት ነው?

ለ) ሰዎች እግዚአብሔርን በሚያመልኩበት ጊዜ ዝንባሌያቸውን ለማስተካከል በቤተ ክርስቲያናችን ለማስተማር የምንችላቸው ነገሮች ምንድናቸው?

አሁንም እግዚአብሔር ለቃየን ተናገረው። ቃየን የሚቆጣበት ወይም የሚቀናበት ምንም ምክንያት እንደሌለው ተናገረው። የቃየንን አምልኮ ተቀባይነት ያለው ለማድረግ እግዚአብሔር ከእርሱ የፈለገው ከሙሉ ልብ የመነጨ መታዘዝን ብቻ ነበር። እንዲሁም እግዚአብሔር ኃጢአት

እንደ ‹አንበሳ› እንደሆነ በመናገር ቃየንን ለመጠንቀቀው። ቃየን ክፉ አመለካከቱን ባይለውጥና ንስሐ ባይገባ፥ ኃጢአት በቃየን ላይ ጌታ በመሆን ያጠፋዋል። ቃየን በንስሐ ወደ እግዚአብሔር ሊመለስና ተቀባይነት ሊያገኝ ይችል ነበር። ጻሩ ግን የቃየን ቁጣ እየባሰ መጣ። በኃጢአትም ተሸነፈና የመጀመሪያው ነፍሰ ገዳይ ሆነ።

የአዳምና ሔዋን ውድቀት ለዘሩ የማይሰጥ ሊመስል ቢችልም፥ የኃጢአት በሽታ በዓለም ውስጥ የማይቋቋሙት ደዌ በመሆን፥ ወደ እያንዳንዱ ቀጣይ ትውልድ ተላለፈ። ቃየን ወንድሙ አቤልን አብሮት ወደ መስኩ እንዲሄድ ጋበዘው። በዚያም በቁጣና በቅንዓት ተነሣሥቶ ገደለው።

ለሁለተኛ ጊዜ እግዚአብሔር ሰውን ከኃጢአቱ በንስሐ እንዲመለስ በማሰብ ሲፈልግ እንመለከታለን። እግዚአብሔር ወደ ቃየን በመሄድ አቤል የት እንዳለ ጠየቀው። ይህም ቃየን አቤልን እንደገደለው እግዚአብሔር ስላላወቀ ሳይሆን፥ ለቃየን ኃጢአቱን የሚናዘዝበትን ዕድል ለመስጠት ነው።

56ኛ ጥያቄ፡- «እኔ የወንድሜ ጠባቂ ነኝን?» ለሚለው የቃየን ጥያቄ ምላሹ ምን ይመስልሀል? ለምን?

«እኔ የወንድሜ ጠባቂ ነኝን?» የሚለው የቃየን ጥያቄ ኃጢአት ያመጣውን የልብ ድንዳኔ ያመለክታል። ንስሐ ያልገባ ልብን በተመለከተ ብዙ ነገሮችን ለመረዳት እንችላለን። በመጀመሪያ ደረጃ፥ ንስሐ ያልገባ ሰው ለእራሱ ብቻ እንጂ ለሌሎች ግድ የለውም። አቤል በመሞቱ ቃየን ቅር አልተሰኘም ነበር። በኋላም በእግዚአብሔር ፍርድ ፊት ቆሞ ሳለ ስለ እራሱ ጉዳዮች ብቻ ያውጠነጥን ነበር። በየትኛውም ሥፍራ ቃየን አቤልን በመግደሉ ሲጸጸት አንመለከትም።

ከየትኛውም ነገድ እንምጣ፥ ሁላችንም የአንድ ቤተሰብ አካላት ነን። ሁላችንም የወንድማችን ጠባቂዎች ነን። ሁል ጊዜም አንዳችን ለሌላችን ግድ መሰኘትና በመንፈሳዊ ሕይወታችን ለማደግ እርስ በእርሳችን መጽናናት አለብን። ይህ ማለት አንዳንድ ጊዜ ሌሎችን ስለ ኃጢአታቸው መገሰጽ ሊሆን ይችላል። እንዲሁም ደግሞ በሥጋዊ

ጉዳት ውስጥ ላሉትም ሊገደንና ልንረዳቸው ይገባል። ምክንያቱም ሁላችንም የአዳም ልጆች ነንና።

57ኛ ጥያቄ፡- ይህ እውነት፡ ሌሎችን በመርዳት ረገድ ዝንባሌያችንን እንዴት ሊለውጠው ይገባል?

የአቤል ንጹሕ ደም በቃየን ላይ ምስክር ነበር። ስለዚህም እግዚአብሔር በቃየን ላይ ፍርድ አመጣ። ቃየን ቤተሰቦቹ ያሉበትን ሥፍራና ያደገበትን አካባቢ እንዲለቅ ታዘዘ። ማረፊያ ቤት የሌለው የምድር ላይ ተቅበዝባዥ መሆን ነበረበት። እህል ለማምረት የሚያደርገው ጥረት ሁሉ በእጥፍ የተረገመ መሆን ነበረበት። ቃየን አዳምና ሔዋን የሚኖሩበትን አካባቢ በመልቀቅ፥ የእግዚአብሔርን የበረከት ሥፍራም እንዳጣ ተገነዘበ።

ሁለተኛ፥ የቃየንን አለመጸጸት ለእግዚአብሔር ከሰጠው ምላሽ ውስጥ እንመለከታለን። ንስሐ ለመግባት ከመሻት ይልቅ፥ ቃየን በእራስ ወዳድነት ለእራሱ ብቻ አሰበ። ከእግዚአብሔርም ጋር መሟገት ጀመረ። የተሰጠው ቅጣት በጣም ከባድ እንደሆነና በሚቅበዘበዝበት ጊዜ የአዳምና ሔዋን ልጆች የአቤልን ሞት ለመበቀል እንደሚገድሉት በመናገር ቅሬታውን ገለጸ።

አሁንም የእግዚአብሔርን ጸጋ እንመለከታለን። እግዚአብሔር በቃየን ላይ የጥበቃ ምልክት አደረገለት። ምልክቱ ምን እንደነበር አናውቅም። ዳሩ ግን ሁሉም ቃየንን ቢገድሉ፥ እግዚአብሔር የከፋ ፍርድ እንደሚያወርድባቸው ተረድተው ነበር። ይሁን እንጂ ቃየን አዳምና ሔዋን ከነበሩበት የበረከት ሥፍራ ለቅቆ መሄድ ነበረበት።

ሦስተኛ፥ የቃየንን አለመጸጸት ለእግዚአብሔር ካለ መታዘዙ እንመለከታለን። መጽሐፍ ቅዱስ ለአዳምና ሔዋን ሦስት ልጆች መወለዳቸውን ብቻ ቢዘግብም፥ ብዙ ወንዶችና ሴቶች ልጆች እንደነበሩዋቸው እናውቃለን (ዘፍ. 5፡4)። ቃየን ከአዳም ልጆች አንዱን አገባ። ሄኖክ (ሄኖሕ) የሚባል ልጅም ተወለደላቸው። ይህ አረማመዱን ከእግዚአብሔር ጋር በማድረጉ ሞትን ሳያይ ወደ ሰማይ የተወሰደው ሄኖክ አይደለም። ለእግዚአብሔር ባለ መታዘዝ፥ ቃየን

ከተማ ሠራ። ተቅበዝባዥ መሆን ሲገባው፥ በከተማ ውስጥ ለመኖር የተቀመጠ ይመስላል።

ቃየንና አቤል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተተኪው ትውልድ ወኪሎች ሆነው ታይተዋል። ቃየን ለእግዚአብሔር ነገሮች ግድ እንደሌለው ሥጋዊ ሰው ሆኖ ታይቷል። አቤል በሙሉ ልባቸው እግዚአብሔርን በመከተል መከራ የሚደርስባቸው ሰዎች ዓይነት ሆኖ ተገልጿል (ዕብ. 11፡4)።

ግድያ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረውን ሰው ማጥፋት ስለሆነ፥ ይህ ታሪክ ግድያ በእግዚአብሔር ዓይኖች ፊት ምንኛ የከፋ እንደሆነም ያስተምረናል። እንዲሁም እርስ በእርሳችን እንድንረዳዳ፥ እግዚአብሔር ከእኛ የሚጠብቀውን መልካም ባሕርይም ያጠፋል። እኛ የወንድማችን ጠባቂዎች ነን።

የዘፍጥረት ጸሐፊ ላሜሕ ወደ ተባለው ሰው እስኪደርስ ድረስ ስለ ቃየን ልጆች በአጭሩ ይናገራል። ዓላማው ኃጢአት እንዴት በአዳም ልጆች ላይ ተጽዕኖ እዳስከተለ ማሳየት ነው። በተለይ ከአዳም ጀምሮ ሰባተኛው የትውልድ ሐረግ ላይ ይገኝ የነበረው ላሜሕ ይህን ክፋት አሳይቷል። አንደኛ፥ ለመጀመሪያ ጊዜ ከአንድ በላይ ሚስት ስለማግባት እናነባለን። ላሜሕ እግዚአብሔር ለአንድ ወንድ አንዲት ሴት አድርጎ ያዘጋጀውን የጋብቻ መስመር በመተላለፍ ሁለት ሚስቶችን አገባ። በብሉይ ኪዳን ታሪክ ሁሉ የእግዚአብሔር ሰዎች ይህንን ልምምድ ቢቀጥሉም፥ የብዙ ጋብቻን አስከፊ ውጤቶች፥ በተለይም በቤተሰብ ሕይወት ውስጥ ለመመልከት እንችላለን።

58ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ብዙ ሚስቶችን ማግባት በቤተሰብ አንድነት ላይ የሚያስከትላቸው አስከፊ ውጤቶች ምንድናቸው?

ለ) የእግዚአብሔር እቅድ አንድ-ለ-አንድ መጋባት እንደሆነ የሚያመለክቱ ጥቅሶች የትኞቹ ናቸው?

ሁለተኛ፥ ላሜሕ ሌላውን ሰው በብቀላ እንደገደለ በድንፋታ ተናግሯል። ንግግሩ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የመጀመሪያው ግጥም እንደሆነ እንመለከታለን (ቁ. 23-24)። የተገደለው ወጣት ምናልባት

ላሜሕን በሙጊያ ውስጥ ያቆነለው ይመስላል። ላሜሕም ለብቀላ ገደለው። ላሜሕ ስለ ፍትሕ ወይም ምህረት የሚገደው ሰው አልነበረም። በድርጊቱ በመጸጸትና በማዘን ፈንታ፥ ሰውዬውን በመግደሉ የራሱን ጀግንነት ተናግሯል። እንዲሁም ደግሞ አቤልን ከገደለው ከቃየን እንደሚበልጥም በትዕቢት ተናግሯል። ላሜሕ በትዕቢት ተገፋፍቶ እርሱና ልጆቹ በቃየን ላይ የተቀመጠውን የእግዚአብሔር እርግማን ከፍጻሜ እንደሚያደርሱ ገልጿል።

59ኛ ጥያቄ፡- የአዘቦት ዓይነት አመለካከት ዛሬ በአብዛኛው የሚታየው እንዲሆን ነው፥

ጽፍጥረት የተጻፈውን ጅማሬ የሚገልጽ መጽሐፍ እንደሆነ ታስታውሳለህ። ከዚህ ምዕራፍ ውስጥ ጅማሬያቸውን እንዳገኙ የተነገረላቸውን የተለያዩ ነገሮች ልብ በል። የቤተሰቦች፥ የከተሞች፥ በርካታ ውስጥ የኖሩ ከብት የሚያግዱ ዘላኖች (በደቡብ ወይም በምሥራቅ አፍሪካ እንዳሉ ዘላኖች)፥ የሙዚቃ፥ የብረታ ብረት ሥራ፥ የብዙ ጋብቻ፥ ወዘተ. ጅማሬ እንመለከታለን። ምንም እንኳ የቃየን ዘሮች ሥልጣኔ ቢጀምሩና ዝነኛና ሀብታም ቢሆኑም፥ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ከእግዚአብሔር የራቁ ነበሩ። ዓለም የሰውን ውጫዊ መከናወን በመመልከት ታጋንናለች። እግዚአብሔር ግን የሰውን ልብ ይመዝናል። እግዚአብሔርን የሚያስደስተውና የበረከት በሩን እንዲከፍት የሚያደርገው፥ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረው እርምጃ እንጂ፥ ቁሳዊ ብልጽግናው አይደለም።

60ኛ ጥያቄ፡- ይህ ዛሬ ባገኘናቸው ስኬታማ ነገሮችና በዓለም ሥልጣኔ ብዙ እንዳንታበይ እንዴት ሊያስጠነቅቀን ይገባል?

ጸሐፊው ስለ ቃየን የሚናገረውን ገለጻ በላሜሕ ታሪክ ይፈጽምና እንደገና ወደ አዳምና ሔዋን በመመለስ፥ ስለ ሦስተኛው ልጃቸው መወለድ ይተርካል። አንዳንዶች የቃየንን ክፋት በማየት ሔዋን አሁን እምነቷን በእዚአብሔር ላይ ጣለች ይላሉ። ከእዚህ በፊት ልጆችዋን ስትሰይም፥ ስለ እግዚአብሔር የሚጠቅስ ነገር አልነበረም። አሁን ግን ስሙ ‹የተሰጠ› የሚል ትርጉም በነበረው በሴት መወለድ፥ እግዚአብሔር የሕይወት ምንጭ እንደሆነ ተረዳች። የበረከት ተስፋውን

በዓለም ለመፈጸም እግዚአብሔር የመረጠው የሴትን የዘር ሐረግ ነው። ሴት የአብርሃምና የኢየሱስ ሥጋዊ አባት ለመሆን በቅቷል።

ምዕራፍ 4 እጅግ ደስ በሚል ዓረፍተ ነገር ይደመደማል። የእግዚአብሔር ምርጥ ዘር በሆነው በሴት መወለድ፥ ሰዎች «የእግዚአብሔርን ስም መጥራት» ጀምረው ነበር። ምንም እንኳ በአዳም ኃጢአት እርምጃቸውን እያፈጠኑ አብዛኛዎቹ ሰዎች ከእግዚአብሔር ቢርቁም፥ እግዚአብሔርን በማሰብና በማምለክ የሚኖር አነስተኛ ቁጥር የነበረው ሕዝብ ነበር። እነርሱም ማምለክ ብቻ ሳይሆን፥ አምላክነቱን ለቀረው የዓለም ሕዝብም አውጀዋል።

አይሁዶች የእግዚአብሔርን ‹ስም› በሚጠቀሙበት ጊዜ የሚያስቡት ስለተጠራባቸው ስያሜዎች (ለምሳሌ ኤሎሂም፥ ወይም ጀሆቫ፥ ወይም ያህዌ) ሳይሆን፥ እንደሁሉን ቻይ፥ ፈጣሪ፥ ፍቅር፥ ወዘተ. ስላሉት ባሕርያቱ ነበር። በኃጢአት ዙሪያቸውን ተከብበው ሳሉ፥ እነዚህ ጥቂት ሰዎች እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል ተረድተው ያመልኩት ነበር። እኛም በዚህ እጅግ በከፋው ትውልድ መካከል፥ እግዚአብሔር ማን እንደሆነ ልናውቀውና ልናከብረው ይገባል።

61ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ከዘፍ. 4 ምን እንማራለን?

ለ) ዛሬ በዓለም የሚገኙ ሰዎች ከቃየንና ከላሜሕ ጋር የሚመሳሰሉት እንዴት ነው?

አምስተኛ ቀን፡-

ለሳምንታዊው ስብሰባ ለመዘጋጀት፥ የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና የመወያያ ጥያቄዎችን ተመልከት።

ሳምንታዊ ስብሰባ

1. ሳምንታዊ የአምልኮ ጊዜ
2. የጸሎት ጊዜ
3. የትምህርቱ ክለሳ
4. የውይይት ጊዜ

ሀ. 1) የአዳምና ሔዋን መፈጠር እግዚአብሔር በጋብቻ ውስጥ ስላለው ዓላማ ምን ያስተምረናል?

2) የኢትዮጵያውያንን ባሕላዊ የጋብቻ አሳብ ከእግዚአብሔር የጋብቻ ዓላማ ጋር አወዳድር። የሚለያዩትና የሚመሳሰሉት እንዴ ነው?

3) የክርስቲያን ጋብቻዎች እግዚአብሔር በጋብቻ ውስጥ ካለው ዓላማ በላይ ባሕላዊ ግንዛቤዎችን የሚያንጸባርቁባቸው መንገዶች ምንድናቸው?

4) ሴቶችና ወንዶች በጋብቻ ውስጥ የሚገኙትን የእግዚአብሔርን ዓላማዎች እንዲያሟሉ፥ ቤተ ክርስቲያንህ እንዴት በተሻለ ሁኔታ ልታዘጋጃቸው ትችላለች?

ለ. 1) በዘፍ. 3፡1-7 ካለው ታሪክ፥ ሰይጣን ሔዋንን ኃጢአት እንድትሠራ ለመፈተን የተጠቀመባቸውን ዘዴዎች ዘርዝር።

2) እኛንም በኃጢአት ውስጥ ለመጣል፥ ሰይጣን ተመሳሳይ ዘዴዎችን የሚጠቀመው እንዴት ነው?

3) ፈተናን እንዴት እንቋቋማለን?

4) ብዙ ክርስቲያኖች በተከታታይ በኃጢአት የሚወድቁት ለምንድነው?

5) የአዳምና ሔዋን የኃጢአት ውጤቶችን ዛሬ በዓለም ላይ እንዴት እንደምንጋፈጥ ግለጽ።

6) ኃጢአታችንን ከተናዘዝን በኋላ እንኳ፥ ውጤቶቹ ብዙውን ጊዜ ቀጣይነት የሚኖራቸው እንዴት ነው?

ሐ. 1) ከውድቀታቸው በፊትና በኋላ፥ እግዚአብሔር በሥራ ላይ ስላለው አመለካከት ከአዳምና ሔዋን ምን ለመማር እንችላለን?

2) ይህ ህብረተሰባችን ዛሬ ሥራን ከሚመለከትበት መንገድ የሚለየው እንዴት ነው?

መ. 1) ኃጢአት ወይም ክፉ ነገር ከሠራን በኋላ ኃላፊነቱን ለመውሰድ የሚከብደን ለምንድነው?

2) በኢትዮጵያ ውስጥ ለነገሮች ማመካኛ ማቅረብ እንዴት እንደሚታይ ምሳሌዎችን ስጥ።

3) እውነተኛ ንስሐ የሚገለጸው እንዴት ነው? ይህን እንዴት እንደተመለከትህ ምሳሌዎችን ስጥ።

4) እውነተኛ ንስሐ ከውሸተኛው እንዴት ይለያል? የሚገለጸውስ እንዴት ነው?

5) ጸሎት።

ትምህርት አራት

ዘፍጥረት 5-9

አንደኛ ቀን፡- ዘፍ. 5-6፡8

ዛሬ በየትኛውም አቅጣጫ ብንመለከት፥ ክፉንም ደጉንም እናያለን። ባልዳኑትም ሰዎች መካከል እንኳ ቸርነትንና የሚያስደንቁ ታላላቅ ሥራዎችን እንመለከታለን። ሰው በቴክኖሎጂ በኩል ያሳየው ችሎታም የሚደነቅ ነው። ዳሩ ግን ትልቅ ክፋትም መኖሩን እንመለከታለን። በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች የሚረግፉባቸው ጦርነቶች ይደረጋሉ። ረሃብ፥ የምድር መናወጥና በሽታም በርክቷል። ለመሆኑ ክፉና መልካም ነገሮች፥ ሁለቱም የሚመጡት ከየት ነው? የዚህ ጥያቄ መልስ በኦሪት ዘፍጥረት የመጀመሪያ አራት ምዕራፎች ውስጥ እንደሚገኝ ባለፈው ሳምንት ተመልክተናል። ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ስለ ተፈጠረ፥ ትላልቅ ነገሮችን የመሥራት ችሎታ አለው። ዳሩ ግን በዙሪያችን ያለማቋረጥ የሚከናወነው ክፉ ሥራ፥ ልክ አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር ላይ እንዳመፁ ሁሉ፥ የዘመኑም ሰው በፈጣሪ አምላኩ ላይ ለማመፁ ምስክር ነው። ሁላችንም በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠርን የአዳምና ሔዋን ልጆች ብንሆንም፥ በኃጢአት እጅግ ተበላሽተናል።

1ኛ ጥያቄ፡- ሀ) የእግዚአብሔርን አምሳል በሰው ሕይወት የሚያንጸባርቁትን ነገሮች ዘርዝር።

ለ) በዓለም ውስጥ የኃጢአትን ተጽዕኖ የሚያመለክቱትን ሌሎች ነገሮች ዘርዝር።